# መጽሐፈ ኢያሱ

ትምህርት ሦስት

## የነገዶች ርስት ክፍፍል

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

© 2017 by Third Millennium Ministries

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form or by any means for profit, except in brief quotations for the purposes of review, comment, or scholarship, without written permission from the publisher, Third Millennium Ministries, Inc., 316 Live Oaks Blvd, Casselberry, Florida 32707.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ **መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ** የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡ ሥርዓተ-ትምህርታችን በአሁኑ ወቅት ከ192 በላይ በሆኑ አገሮች ውስጥ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ጎብኙ፡፡

**ማውጫ**


1. **መግቢያ**
2. **የመነሻ ድንበሮች**
   ሀ. አወቃቀርና ይዘት
   1. ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉ ድንበሮች
   2. ከዮርኖስ መለስ ያሉ ድንበሮች

   ለ. ቀደምት ትርጓሜ
   1. መለኮታዊ ሥልጣን
   2. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን
   3. የሙሴ ህግ ስነ-ልክ
   4. የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል
   5. አስራኤል በጠቅላላ
3. **ለየት ያለ ድልድል**
   ሀ. አወቃቀርና ይዘት
   1. የመግቢያ ማጠቃለያ
   2. የመዝጊያ ማጠቃለያ
   3. ይሁዳ
   4. ኤፍሬምና ምናሴ
   5. ትናንሾቹ ነገዶች
   6. ሌዊ

   ለ. ቀደምት ትርጓሜ
   1. መለኮታዊ ሥልጣን
   2. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን
   3. የሙሴ ህግ ስነ-ልክ
   4. የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል
   5. እስራኤል በጠቅላላ
4. **ብሔራዊ አንድነት**
   ሀ. አወቃቀርና ይዘት
   1. የመሠዊያ ግንባታ
   2. የጦርነት ትንኮሳ
   3. ፍልሚያ
   4. የትኮሳው መርገብ
   5. የመሰዊያው ስያሜ

   ለ. ቀደምት ትርጓሜ
   1. መከኮታዊ ሥልጣን
   2. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን
   3. የሙሴ ህግ ስነ-ልክ
   4. የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል
   5. እስራኤል በጠቅላላ
5. **ክርስቲያናዊ ተዛምዶ**
   ሀ. ብሥራት
   ለ. መስፋፋት
   ሐ. ፍጻሜ
6. **ማጠቃለያ**

# የመጀመሪያው ድንበር

ቀደም ባለው ትምህርታችን እንደተመለከትነው፣ እስራኤል ለኢያሱ በተገባለት ተስፋ መሠረት እጅግ ሰፊ የሆነ ግዛትን እንደወረሰች የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ ተረድቷል፡፡ ይህ ውርስ፣ እግዚአብሔር መላውን ዓለም ለመውረስ ያለውን እቅድ ለሰው ልጆች ሁሉ የሚቀርበው ዘላቂነት ያለው ልዩ ጥሪ አካል ነው፡፡ አሁን ቀጥሎ እንደምንመለከተው፣ በኢያሱ ዘመን፣ እስራኤል ለአባታቸው ለአብርሃም በተገባው ተስፋ መሠረት ሁሉንም ርስታቸውን አለመውረሳቸውንም የመጽሐፋችን ጸሐፊ እንደተገነዘበም እንረዳለን፡፡ ይልቁኑ፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ከዚያ ሰፊ ርስት በጥቂቱ ውስጥ ጽኑ ቁመና እንዲኖራት የሚያስችላትን ስፍራ እንድትይዝ አድርጓል፡፡ ሆኖም፣ ከጸሐፊአችን እይታ አንጻር ስንቃኘው፣ በየዘመናቱ የሚመጣው ትውልደ እስራኤል እነዚያን ተለይተው የተሰጡትን መሬቶች በማወቅ የማስከበሩ ነገር እጅግ ወሳኝ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ይህንን የእስራኤልን ቀዳሚ ድንበር ዘገባ በሁለት ክፍለን እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ መሠረታዊ አወቃቀሩንና ይዘቱን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ የዚህን ክፍል ተቀዳሚ ትርጉም ወደመመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡ አስቀድመን አወቃቀሩንና ይዘቱን እንመልከት፡፡

## አወቃቀርና ይዘት

ይህኛው የኢያሱ መጽሐፍ ክፍል በሁለት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ 13፡1-7 ከዮርዳኖስ ወዲህ ባለው የእስራኤል ድንበር፣ ማለትም ከዮርኖስ ወንዝ በስተምዕራብ ወገን ባለው የከነዓን ምድር ላይ ያተኩራል፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ 13፡8-14፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ባለው የእስራኤል ድንበር ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ይህም በዮርኖስ በስተ ምሥራቅ የሚገኘውን ድንበር የሚመለከት ይሆናል፡፡

ይህንን የኢያሱን መጽሐፍ ክፍል ቀረብ ብለን ስንመለከተው፣ የእስራኤልን ርስት ድንበር ቀደምት ዳራ በልቡናችን ውስጥ ማድረግ እጅግ ያስፈልገናል፡፡ በዘፍጥረት 15፡18-21 ውስጥ፣ "ከግብጽ ድንበር አንስቶ" እስከ ምዕራባዊው ዳርቻ ድረስ የሚዘልቅ ርስት እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ ሊሰጥ ተስፋ ገባላቸው፡፡ የግብጽ ዳርቻ ወይም ወንዝ ተብሎ የተጠቀሰው በአሁኑ ወቅት የማይገኘው የዓባይ ወንዝ ምሥራቃዊ ቅርንጫፍ አሊያም፣ የኤል-አሪሽ ዋዲ በአሁኑ ወቅት የምናገኘው ከዓባይ በስተምሥራቅ የሚገኘው ክፍል ሊሆን ይችላል፡፡ በስተሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ ደግሞ፣ ለአብርሃም ተስፋ የተገባለት ምድር እስከ "ታላቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ" ድረስ ይዘልቃል፡፡ ከዚያ አንስቶ፣ እስራኤል የእግዚአብሔርን በረከት ወደ መላው ዓለም ታደርሳለች፡፡ ወደ እውነታው ስንመጣ ግን፣ የዳዊት መንግሥት እስኪመጣ ድረስ የእስራኤል ድንበር በዚያ ልክ አልተስፋፋም ነበር፡፡ በኢያሱ ዘመን፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጣት በከፊል ሲሆን፣ ከዮርዳኖስ ማዶና መለስ ባሉት ግዛቶች ለቅምሻ ያህል ወርሰው ነበር፡፡ መጽሐፋችን እንደሚያመለክተን ግን፣ በእነዚህ ምድሮች ውስጥ በአስተማማኝነት መቀመጥ ለእስራኤላውያን ወሳኝ የመጀመሪያ እርምጃ ነበር፡፡

> *ከአብርሃም ጀምሮ፣ እግዚአብሔር ህዝብ እንደሚያመጣ፣ ያም ህዝብ ለምድር ሁሉ በረከት እንደሚሆንና የሚጫወተውም ወሳኝ ሚና እንዳለው ተስፋን ሰጥቶ ነበር፡፡ እነዚያ ህዝቦች፣ ግብጽን ለቅቀው ሲወጡና ምድሪቱን ሲወርሱ፣ የሚገባቸው እንዳልሆነ የተረዱ ሰዎች ነበሩ፡፡ ምድር በተሰኘችው ፕላኔት ውስጥ፣ የይገባኛል ጥያቄ ሊያቀርቡበት የማይችሉትን፣ መብታቸውም ሊሆን የማይችለውን ነገር እግዚአብሔር ግን እርሱ በሰጠው ተስፋ መሠረት ብቻ እርሱም ብቻውን ወደ ፍጻሜ ሊያመጣው የሚችለውን ምድር ሰጣቸው፡፡*
>
> *ዶ/ር ዳግላስ ስቱዋርት*

## ከዮርኖስ መለስ ያሉ ደንበሮች

ከዮርዳኖስ መለስ ያሉ ድንበሮች ትረካ የሚጀመረው በምዕራፍ 12 ላይ ኢያሱ ድል አድርጎ በወረሳቸው ግዛቶች ዝርዝር ላይ ተመሥርቶ ነው፡፡ በ13፡1 ላይ "ኢያሱም ሸመገለ በዕድሜም አረጀ" በማለት ይጀምርና "ያልተወረሰች እጅግ ብዙ ምድር ገና ቀርታለች፤" ብሎ ይደመድማል፡፡ ያልተወረሰው ምድር በከነዓን ሰሜናዊ ምድር ውስጥ የሚገኘው የፍልስጥኤማውያን ምድር ነው፡፡ በ13፡6 ውስጥ፣ "እነዚህን ከእስራኤል ልጆች ፊት አባርራቸዋለሁ፤" በማለት

እግዚአብሔር ራሱ ተስፋ ሰጥቷል፡፡ ስለዚህ፣ በቁጥር 7 ውስጥ፣ ኢያሱ ወደፊት እንዲገፋና የከነዓንን ምድር እንደ እስራኤል ርስት አድርጎ እንዲቆጥር እግዚአብሔር ያዝዘዋል፡፡

## ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉ ድንበሮች

በሁለተኛው ክፍል፣ በ13፡8-14 ውስጥ፣ ጸሐፊአችን ስለ እስራኤል ቀደሚ ውርስ የጀመረውን ዘገባ ንድፉን ያጠናቀቀው ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉትን ውጫዊ ድንበሮች ማለትም ከዮርዳኖስ ምስራቅ ያሉትን ምድሮች በመዘርዘር ነው፡፡ ጸሐፊአችን ዘገባውን የሚጀምረው በ13፡8 ውስጥ ሙሴ ከመሞቱ አስቀድሞ እነዚህን ድንበሮች የእስራኤል ግዛት አድርጎ እንዳስቀመጣቸው በማስታወስ ነው፡፡

በዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ የሚገኘው የእስራኤል ተቀዳሚ የነገዶች የርስት ክፍፍል የሚስፋፋው በስተደቡብ እስከ ሞዓብ ድረስ ደግሞም በስተሰሜን እስከ ሄርሞን ተራራ ድረስ ነው፡፡ ነገር ግን በ13፡13 ውስጥ ጸሐፊአችን እንደዘገበው እስራኤላውያን ከምድሪቱ ያላስወጧቸው ቡድኖች ነበሩ፣ እነርሱም፣ "ጌሹራውያንና ማዕካታውያን" ናቸው፡፡ ይህም ሆኖ ግን፣ ምድሪቱ በጠቅላላ  በኢያሱ ዘመን ለእስራኤላውያን ውርስ ተደርጋ እንደተሰጠች ሙሴ አስረግጦ ይናገር ነበር፡፡  ጸሐፊአችን በተቻለው መጠን ሁሉን ለማካተት ባደረገው ጥረት፣ በ13፡14 ላይ በቅንፍ ውስጥ የሚቀመጥ ሃሳብ የሚመስል ጽሑፍ አስሯል፡፡ ሌዋውያንም ድርሻ ተሰጥቷቸዋል፣ የእነርሱ ግን ከመሬተረ ይልቅ "ለእግዚአብሔር የቀረበው በእሳት የተደረገ መሥዋዕት ነው" በማለት ማብራሪያ ሰጥቶበታል፡፡

> *በኢያሱ መጽሐፍ የመልክዓ ምድር ጉዳይ እጅግ ወሳኝ ነገር ነው፣ ደግሞም የየምድሮቹ ወሰን ደግሞ ለእርሱ እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ነገር ነው፣ በተለይ ደግሞ ከተራሮች ጋር የተያያዘው ነገር ማለት ነው፡፡ ያደርጉ የነበረው ምንድን ነው? የተቀደሰው ምድር ድንበር ምን ሊሆን እንደሚገባው ድንበር ማበጀት ሲሆን፣ ያም ምልክታቸው ይሆናል ማለትም ከዚያ ተነስተው ቀጣዩን ያመለክታሉ፡፡ በተለምዶ የእስራኤል ሰሜናዊው ድንበር ምልክት የሄርሞን ተራራ ነው፡፡ ከዚያ ደግሞ የእስራኤል ምሥራቃዊ ድንበር በተራሮች ላይ ይመሠረታል፣ በተለይም በስተደቡብ ኤዶም፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ የሞዓብ ከፍተኛ ስፍራዎች፣ ተራሮቹ፣ የኮረብታ መስኮቹ፣ እና የሞዓብና የባሳን ኮረብታማ ምድር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ፣ በዛሬው ዘመን ዮርዳኖስን ዳር እስከዳር ማለትም ከሰሜናዊው ዮርዳኖስ እስከ ደቡባዊው ዮርዳኖስ ያለውን የሚያካትት ሲሆን የምድሪቱን ምሥራቃዊ ድንበሮች ያበጃል ማለት ነው፡፡*
>
> *ዶ/ር ቶም ፒተር*

የእስራኤልን ርስት የመጀመሪያ ድንበር መሠረታዊ አወቃቀርና ይዘት በልቡናችን አድርገን፣ የጥቅሶቹን ቀደምት ትርጓሜ ወደ መመርመሩ እንሸጋገራለን፡፡ ጥያቄአችንም፡ ጸሐፊአችን በዚያን የታሪክ ዘመን ውስጥ የእስራኤልን ርስት ንድፍ በመግለጽ የዚህ ክፍል ዘገባውን ሊጀምረው ለምን ወደደ?

## ቀደምት ትርጓሜ

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፣ እስራኤላውያን በመሳፍንት ዘመን፣ በነገሥታት ዘመንና በባቢሎን ምርኮ ዘመን፣ እግዚአብሔር የሰጣቸውን የርስት ድንበር ለማስከበር፣ አስጠብቆ ለማቆየትና ለመቆጣጠር ፈተና ገጥሟቸው እንደ ነበር ማስታወስ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ በእስራኤል ነገዶች መካከል ያለ ግጭት፣ በምድሪቱ ውስጥ ከሚኖሩ ህዝቦች የሚመጣ ችግር፣ በምድረበዳ ካሉ ነገዶች የሚመጣ ጥቃት፣ በስተመጨረሻም ግብጽን፣ አሶርን እና ባቢሎንን ከመሳሰሉ ታላላቅ አገሮች የሚመጣ የወረራ መቅሰፍት፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም በሰጠው ተስፋ መሠረት እስራኤል ርስቷ ላይ እንዳትጸና ያላትም እያደር እንዲሸረሸርና እንዲቀንስ ያደርገዋል፡፡

ጸሐፊአችን ለተደራሲያኑ የድንበራቸውን ክልል በማሳሰብ፣ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ድንበር ማስከበርና ተጠብቆ እንዲቆይ የማድረጉ ነገር ለእነርሱ ምን ያህል ፋይዳ እንዳለው ያመለክታቸዋል፡፡ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን በረከት ለመላው ዓለም ማስፋፋት የሚችሉት ከተሰጣቸው ተነስተው ወደፊት በመግፋት በርካታ ምድሮችን መውረስ ከቻሉ ብቻ ነበር፡፡

ተደራሲያኑ አስቀድሞ ለእስራኤል የተሰጠውን ድንበር ጨርሰው ሊዘነጉት እንደማይገባ ለማሳመን ሲል፣ ጸሐፊአችን ቀደም ባሉት ምዕራፎች ያሰመረባቸውን አምስት መሪ ሃሳቦች በእነዚህም ምዕራፎች ውስጥ አሰካክቶ በማቅረብ የነገሩን ወሳኝነት አመልክቷል፡፡

## መለኮታዊ ሥልጣን

በመጀመሪያ ደረጃ፣ መለኮታዊ ሥልጣን የእስራኤልን ርስት እንዴት እንዳጸናው ያመለክታቸዋል፡፡ አስቀድሞ በ13፡1 ላይ ከዮርዳኖስ መለስ ባሉ ግዛቶች ላይ በማተኮር "እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው" ይላል፡፡ ደግሞም በ13፡6 ውስጥ፣ "እንዳዘዝሁህም ምድራቸውን ለእስራኤል ርስት አድርገህ አካፍላቸው።" በማለት እግዚአብሔር ለኢያሱ ያዘዘውን ዘግቦልናል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ መለኮታዊው ሥልጣን ከእስራኤል ወዲያ ባሉ አገሮችም የሚገኙትን የእስራኤል ድንበሮች አጽንቷል፡፡ በ13፡8 ውስጥ "በዮርዳኖስ ማዶ ሙሴ የሰጣቸውን ርስታቸውን" ተብሎ ተጽፎ እናነብባለን፡፡

እስራኤላውያን ተስፋ ከተገባላቸው ምድር ከፊሉን ብቻ ወርሶ የመቀመጡ ነገር ምን ያህል እንደሚቀልላቸው የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ ያውቃል፡፡ ስለዚህ፣ ወደፊት የሚመጡት የእስራኤል ትውልዶች እነዚያን ምድሮች ሙሉ በሙሉ የመውረስ ወኔ ካጡና በትንሹ ረክተው ከተቀመጡ፣ ከእግዚአብሔር ሥልጣን በተቃራኒው እንደሚሰለፉና እርሱ የሰጣቸውን የውክልና ሥልጣናቸውን እንደሚያቃልሉ ግልጽ አድርጎ ያስቀምጥላቸዋል፡፡

### የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን

በሁለተኛ ደረጃ፣ ለእስራኤል የተሰጣት ተቀዳሚ ድንበሮች እግዚአብሔር ለእስራኤል በገባው ቃል ኪዳን የጸና መሆኑን የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ ያመለክታል፡፡ ከዮርዳኖስ መለስ ያሉትን አስመልክቶ፣ በ13፡6 ውስጥ የከነዓን ምድር በጠቅላላ ለእስራኤል "ግዛት" ወይም በዕብራይስጡ "*nachalah*" (**נַחֲלָה**) ተደርጎ የተሰጠ መሆኑን እግዚአብሔር ያብራራል፡፡ ቀደም ባሉት ትምህርቶች እንዳመለከትነው፣ እነዚህን ድንበሮች የእስራኤል ግዛቶች ናቸው ብለን ዘግበናል ምክንያቱም ለአብርሃም በተገባው ቃል ኪዳን ውስጥ፣ እነርሱ ለእስራኤል ዘላቂ ርስት እንደሚሆኑ እግዚአብሔር ተስፋን ሰጥቷል፡፡ በሲና ተራራ ላይ ከሙሴ ጋር ባደረገው ቃል ኪዳን ውስጥም እነዚህን ተስፋዎች እግዚአብሔር ማረጋገጫ ሰጥቶባቸዋል፡፡ በ13፡8 ውስጥም በተመሳሳይ መንገድ፣ ከእስራኤል ማዶ ያለውም ግዛት የእስራኤል ርስት ተብሎ ተጠቅሷል፡፡

በዚህ መንገድ ትኩረት ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ እንዲሆን በማድረጉ፣ የጸሐፊአችን መልእክት ምንም እንከን የሌለው ይሆናል፡፡ በየትውልዱ የሚመጡ እስራኤላውያን በጠቅላላ የእስራኤል ርስት፣ ግዛቶቿን የማስከበሯና የመቆጣጠሯ ነገር እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው በገባው የተቀደሰ ቃል ኪዳን የጸና መሆኑን እውቅና ሊሰጡት ገባል፡፡

> *በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ፣ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ቃል ኪዳን ሲገባ፣ አራት ነገሮችን ሊያደርግለት እውነተኛ ተስፋ ሰጥቶት ነበር፡፡ ቁጥራቸው በሰማይ እንዳለ ከዋክብት፣ በባህር እንዳለ አሸዋ እስኪሆን ድረስ ብዙ ትውልዶችን እንደሚሰጠው ተስፋን ሰጠው፡፡ እንደሚጠብቃቸው፣ አምላካቸው እንደሚሆን፣ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን እና እንደሚያበለጽጋቸው ተስፋን ሰጣቸው፡፡ በእርግጥም፣ ለአህዛብ ሁሉ በረከት እንደሚሆኑ፣ ያም መሲህዊ ተስፋ እንደሆነ እና መሲሁም ከአይሁድ ህዝብ፣ ማለትም ከእብራውያን ወገን እንደሚሆን ጭምርም ተስፋን ሰጣቸው፡፡ በአራተኛ ደረጃ ደግሞ፣ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ህዝቡ የራሳቸው የሆነ ርስት እንደሚኖራቸው፣ ያም ርስት የከነዓን ምድር እንደሆነ ተስፋን ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህ ነገር ለእስራኤል ህዝብ የተሰጠ ጥቅል ተስፋ ብቻ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ህዝብ ውስጥ ለሚገኝ ለእያንዳንዱ ነገድ በተናጠል፣ የየራሱ ርስት እንደሚኖረው የሚያረጋግጥም ጭምር ነው፡፡*
>
> *ሬቨረንድ ኬቪን ላቢ*

## የሙሴ ህግ ስነ-ልክ

በሦስተኛ ደረጃ፣ የእስራኤል የመጀመሪያ ድንበር ዘገባ አጽንዖት ያደረገው ግዛቶቹ በሙሴ ህግ ስነ-ልክ መሠረት የተረጋገጡ መሆናቸውን ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ከዮርዳኖስ መለስ ስላሉት ግዛቶች በሚናገረው ክፍል መግቢያ፣ በ13፡1 ውስጥ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል፡ "ያልተወረሰች እጅግ ብዙ ምድር ገና ቀርታለች፤" ይህ ነገር አዲስ መገለጥ አይደለም፡፡ ዘዳግም 20፡16-17 በመሳሰሉት ምንባቦች ውስጥ እስራኤላውያን እነዚያን ምድሮች እንዲወርሱ ሙሴ ባዘዘው ትዕዛዝ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድም፣ በ13፡8 ውስጥ፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ስላሉትም ግዛቶች እንዲህ ተብሏል፡ "በዮርዳኖስ ማዶ ሙሴ የሰጣቸውን ርስታቸውን ተቀበሉ።" የሙሴ ህግ ዘኍልቁ 32፡33-42 እና ዘዳግም 3፡8-17 በመሳሰሉት ክፍሎች እንደተጠቀሰው የሙሴ ህግ በዮርዳኖስ አካባቢ ያሉትን ግዛቶች እንደሚወርሱ ተረጋግጧል፡፡

የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ ከተደራሲያኑ መካከል አስቀድሞ የተሰጣቸውን የየነገዳቸውን ርስት ከመውረስ አንፃር ብዥታ ያለባቸውን ሁሉ ለማሳመን ሲል ትኩረቱን በሙሴ ህግ ላይ አድርጓል፡፡ እንዲያውም ሙሴ ራሱ ግዛቶቻቸውን እንዲቆጣጠሩ ለእስራኤላውያን ትዕዛዝ አስተላልፏል፡፡

## የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሯዊ ኃይል

በአራተኛ ደረጃ፣ ጸሐፊአችን ስለ እስራኤል የመጀመሪያ ርስትና ድንበር በሚያወሳበት ወቅት፣ በእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሯዊ ኃይል ላይ ትኩረት እንዲደረግ አሳስቧል፡፡ በ13፡6 ውስጥ ከእስራኤል መለስ ስላሉ ግዛቶች ሲጽፍ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል፡ "እነዚህን (የቀሩትን ከነዓናውያንን ሁሉ) ከእስራኤል ልጆች ፊት አባርራቸዋለሁ፤" ከዮርዳኖስ ማዶ ስለሚገኙት ግዛቶች በዘገበበት ክፍል ውስጥ፣ ግዛቶቹን የመውረሱ ነገር የሚጸናው እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል መሠረት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በ13፡10 ውስጥ፣ ተዓምራዊ የሆነውንና "በአሞራውያን ንጉሥ በሴዎን" ላይ የተገኘውን ድል እንደገና ያሳስባል፡፡ ደግሞም በቁጥር 12 ውስጥ፣ "በባሳን ንጉሥ በዐግ" ላይ የተገኘውን ተዓምራዊ ድልም ያሳስባል፡፡

ቀደምት ተደራሲያኑ ተስፋቸውን ሊያደርጉ የሚገባው በእነርሱ ምትክ በሚገለጠው መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት እንዲሆን እነዚህ ሁለቱም ክፍሎች ያመለክታሉ፡፡ ከዮርዳኖስ መለስና ከዮርዳኖስ ማዶ የሚገኙትን ግዛቶች የመውረስ ተስፋቸው እውንና እርግጠኛ የሚሆነው ያ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

## እስራኤል በጠቅላላ

በአምስተኛ ደረጃ፣ የእስራኤል የመጀመሪያ ድንበር ዘገባ እስራኤል በጠቅላላ የመሳተፋን አስፈላጊነትም ያተኮረበት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ኢያሱ 13፡7 እንደዘገበው፣ ከዮርዳኖስ መለሰ ያሉት ግዛቶች "ለዘጠኙ ነገድ ለምናሴም ነገድ እኩሌታ" ርስት አድርገህ ስጥ ይላል፡፡ በኢያሱ 13፡8 ደግሞ፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ያለው ግዛት "ከምናሴ ጋር የሮቤልና የጋድ ልጆች" እንዲካፈሉት እንደተሰጠ ተጠቅሷል፡፡ እስራኤል በጠቅላላ የተሰኘውን መሪ ሃሳብ ሲያሰምርበትም፣ በ13፡14 ላይም ለሌዊ ነገድ ልዩ ርስት ተደርጎ የተሰጠው ተጠቅሷል፡፡

ደግሞ ደጋግሞ በአጽንኦት እንደገለጸው፣ የጸሐፊአችን ቀደምት ተደራሲያን የሆኑት የእስራኤል ነገዶች በአንድነት መቆም እንደሚገባቸው በግልፅ አስቀምጧል፡፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ሁለቱም አቅጣጫ ህልውናቸውንና ቀደም ብሎ የነበራቸውን ገዢነታቸውን ለማስከበር የእግዚአብሔር ህዝብ አንድነት እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

የእስራኤልን ነገዶች የርስት ክፍፍል ከተመለከትን፣ በዚህ ትምህርት ሁለተኛው ዋና ርእሳችን ወደሆነው ርዕስ እንሸጋገራለን፡፡ እነዚህ ርስቶች ለእያንዳንዱ ነገድ ለየት ባለ መንገድ እንዴት እንደተከፋፈለ እናያለን፡፡ እነዚህ መሬቶች እንዴት ነው የተከፋፈሉት?

## ለየት ያለ የርስት ክፍፍል

ጸሐፊአችን በዚህኛው የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ፣ የእስራኤልን ድንበሮች ከመግለጽ ባሻገር ለየት ላሉ ነገዶች በተለየ ሁኔታ በተደረገው የርስት ክፍፍል ላይ አትኮሮት አድርጎ ዘግቧል፡፡ በቅርቡ እንደምንመለከተው፣ እነዚህ ድልድሎች ችግር ያስከተሉ ናቸው ምክንያቱም አንዳድ ነገዶች ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ ሰፋ ያሉ ድርሻዎችን ስለወሰዱ ነው፡፡ የመሳፍንት፣ የሳሙኤል እና የነገሥት መጻሕፍት እንደሚነግሩን፣ እነዚህ  ለየት ያሉ ክፍፍሎች አለመተማመንን፣ አንዱ አንዱን መበደልን፣ መከፋፈልን አልፎም በነገዶች መካከል ጦርነትን ቢቀሰቅሱ እስገራሚ አይሆንም፡፡ ቀደምት ተደራሲያኑ እነዚህን ችግሮች ሲጋፈጡ ሊያደርጉ የሚገባቸውን ነገር ላማሳየት ሲል በኢያሱ ዘመን እግዚአብሔር የሰጣቸውን እነዚህን ለየት ያሉ ክፍፍሎች እንዲያውቁና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያሳስባቸዋል፡፡

ጸሐፊአችን በእስራኤል የርስት ክፍፍል ውስጥ እነዚህን ለየት ያሉ ድልድሎች የዘገበበትን መንገድ በለተመደው መንገድ ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ መሠረታዊ አወቃቀሩንና ይዘቱን እንመረምራለን፣ ሁለተኛ ደግሞ፣ ቀደምት ትርጓሜውን እንዳስሳለን፡፡ አስቀድመን ወደዚህ የኢያሱ መጽሐፍ ክፍል አወቃቀርባ ይዘት እንሸጋገርና እንመልከተው፡፡

## አወቃቀርና ይዘት

በ13፡15-21፡45 በሚገኘውና የእስራል ነገዶች ለየት ያለ የርስት ክፍፍል ውስጥ፣ ረጃጅም የህዝብ፣ የክልል፣ የዋና ከተሞች፣ የትናንሽ ከተሞች እና የመንደሮች ዝርዝሮች የሰፈሩ ሲሆን እርስ በርሳቸው የተያያዙ አጫጭር ታሪኮች እዚህም እዚያም ተሰበጣጥረው በመቀመጣቸው ግራ አጋቢ ገጽታ አላቸው፡፡ በእነዚህ ሁሉ የተለያዩ ታሪኮች ውስጥ የተቀመጠውን ዋና ሃሳብ ለመረዳት ያስችለን ዘንድ በሁለት ዋና አንጓዎች መክፈል ይረዳናል፡፡ በ13፡15-33 የሚገኘውና ከዮርዳኖስ ማዶ ሙሴ ለእራኤል ነገዶች የሰጠው የርስት ድልድል፣ እና ከዮርዳኖስ መለስ ኢያሱ ለነገዶቹ የሰጠውና ረዘም ያለ ስፍራ የያዘው የነገዶች የርስት ክፍፍል የተመዘገበበት  በ14፡1-21፡45 የሚገኘው ክፍል ነው፡፡

ከዮርዳኖስ ማዶ የተሰጠው የነገዶች የርስት ክፍፍል አጠር ያለው ነው፡፡ የሚጀምረውም በ13፡15-23 በሚገኘው የሮቤል ነገድ ነው፡፡ የጋድ ነገድ ክፍፍል ደግሞ በቁ24-28 ውስጥ ይገኛል፡፡ ከዮርዳስ ማዶ የምናሴ ነገድ እኩሌታ የርስት ክፍፍል ደግሞ ከቁ 29-31 ውስጥ ይገኛል፡፡ ከዚያም ጸሐፊአችን በቁጥር 32 እና 33 ውስጥ ለሌዊ ነገድ የተሰጠውን ለየት ያለ ድልድል በመዘገብ ይህንን ክፍል ያጠናቅቅና ወደሚቀጥለው ክፍል ይሸጋገራል፡፡

> *የሌዊ ነገድ ለመላው የእስራኤል ህዝብ የክህነት አገልግሎትን ለመስጠት በመመረጡ ምክንያት ነገዱ በመደበኛው የርስት ክፍፍል ውስጥ ተካትቶ ርስት አልተቀበለም፡፡ በኢያሱ 13 ውስጥ እግዚአብሔር ርስታቸው እንደሆነ ተመዝግቦ እናገኛለን፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የሌዊ ነገድ ከዐሥራሁለቱ የእስራኤል ነገዶች የርስት ክፍፍል ውስጥ ተካትቶ አናገኘውም፣ ስለዚህ የሌዊ ነገድ ድርሻው እስራኤላውያን የሚያቀርቡት መስዋዕት፣ ማለትም የእስረኤል ህዝብ ከሚያመጣው ዐሥራትና መባ ውስጥ የሚወሰድ ይሆናል ማለት ነው፡፡*
>
> \- *ሬቨረንድ ሄነሪ ቱርካኒክ፣ ተተርጉም የቀረበ*

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ፣ ጸሐፊአችን ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ ያሉ ምድሮች ለሮቤል፣ ለጋድ እና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ እንዴት አድርገው በጥንቃቄ እንደተከፋፈሉና እንደተከለሉ ጠቅሶልናል፡፡ ጥቅል በሆነው አተያይ ሲታይ፣ ክፍፍሉ ግልፅ ይመስላል፣ ለየነገዶቹ ግን ክፍፍሎቹ ቀጥተኝነት የጎደላቸው ይመስላሉ፡፡ አንደኛው ድንበር ከሌላኛው ጋር ከመቀራረቡ

የተነሳ በሚነሱ የድንበር ግጭቶች ምክንያት ጸሐፊአችን የትኛው ክልል፣ ከተማና መንደር ለማን እንደተሰጠ ለማመልከት ሲል አንዳን ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ሲሰጥ እናስተውላለን፡፡

*የዘመናችን ክርስቲያኖች የኢያሱን መጽሐፍ ከምዕራፍ 13-22 በሚያነቡበት ወቅት፣ የእኛ ቀልብ እምብዛም ሊስብ የማይችሉ ሃሳቦችን በማንበብ ፈተና ውስጥ ይገባሉ፡፡ ሃሳቦቹም ለዚህ ነገድ ከዚህ እስከዚህ፣ ለዚያኛው ደግሞ ከዚህ እስከዚያ፣ ይህኛው ከተማ ለዚህ ያኛው ደግሞ ለዚያ እያለ የተቀመጠውና በጣም ረጃጅም የድንበር ዝርዝሮችን ያሰፈረው ክፍል ውስጥ የሚገኙት ናቸው፡፡ በመሠረቱ፣ ከዘመናችን ሰዎች አንዳንዶቹ ይህንን ክፍል በሚያነብቡበት ወቅት፣ ክፍሉን ያዩትና፣ "ይህ ነገር ከሃይማኖት ጋር ምን ያገናኘዋል?" ወይም "ለመሆኑ ይህ ጉዳይ ለእምነት ምን የሚፈይደው ነገር አለ?" ይላሉ፡፡ ሆኖም ግን፣ በመጽሐፈ ኢያሱ ተቀዳሚ መቼት አንፃር ስንመለከተው፣ ጉዳዩ ከእስራኤላውያን እምነትና ከእግዚአብሔር ጋር ከሚኖራቸው እርምጃ አንፃር በግል እንደነገድ፣ ከዚያም እንደ አንድ ህዝብ የሚመለከታቸው ብርቱ ጉዳይ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ፣ በዓለም ውስጥ ከሚገኘው ግዛቱ ኢያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ የት መስፈርና መኖር እንዳለበት ስለ ደነገገ ነው፡፡ ርስቱም ቋሚ ሲሆን፣ እንዲያውም የገዛ ምድራቸው፣ ማለትም ለእስራኤል በጠቅላላ የኔ ብሎ የሚጠራው ምድር እንዲሆን የተሰጠ ምድር ስለሆነ ነው፡፡*

*ዶ/ር ሪቻርድ ኤል. ፕራት፣ ዳግማዊ*

ከዚህ በመቀጠል፣ ጸሐፊአችን ሰፋ ያለ ስፍራ በመስጠት ከዮርዳኖስ መለስ ኢያሱ ለእያንዳንዱ ነገድ የሰጠውን ለየት ያለ የርስት ክፍፍል በዝርዝር ዘግቦልናል፡፡ ይህ ክፍል በስድት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡

## ጠቅለል ያለ መግቢያ

ይህ ክፍል የሚጀምረው አስቀድሞውኑ ሙሴ ከዮርዳኖስ ማዶ ባሉት ምድሮች ያደረገውን ነገር በምዕራፍ 14፥1-5 ውስጥ ጠቅለል ያለ መግቢያ በመስጠት ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ከዮርዳኖስ መለስ በሚኖሩት ምድሮች ውስጥ ኢያሱ የሚያደርገው የርስት ማከፋፈል ሥራ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊሆን እንደሚገባው ከአንድ ጊዜ በላይ አጽንዖት ተሰጥቶበታል፡፡

## ጠቅለል ያለ መዝጊያ

ከመጀመሪያው ክፍል ጋር በተመጣጠነ መንገድ፣ በምዕራፍ 21፥43-45 የሚገኘውና ከዮርዳኖስ መለስ ያለው የርስት ክፍፍል የተዘገበበት የመዝጊያው ክፍል ነው፡፡ በ21፥43 ውስጥ ጸሐፊአችን "ለአባቶቻቸው የማለላቸውን ምድር ሁሉ ለእስራኤል ሰጠ፤ ወረሱአትም፥ ተቀመጡባትም።" በማለት ያብራራልናል፡፡ ከዚያም ሁኔታው እንዴት አግባብት እንዳለው ለማሳየት ለተደራሲያኑ ለማሳየት ሲል ጸሐፊአችን ይህንን ክፍል በቁጥር 45 "እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት ከተናገረው መልካም ነገር ሁሉ ተፈጸመ እንጂ ምንም አልቀረም።" በሚል አዋጅ ያጠቃልለዋል፡፡

በኢያሱ 13 – 22 ውስጥ፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠው የቃል ኪዳን ተስፋ ተፈጽሞ እናገኛለን፣ ምክንያቱም በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ምድሪቱ ለዐሥራሁለቱ የእስራኤል ነገዶች በተመጣጠነ መንገድ እንዴት እንደተከፋፈሉ በዝርዝር ተመዝግቦ ስለምናገኝ ነው፡፡ በተለይም 21፥45 ሊጠቀስ የሚገባው ነው፡፡ በዚያም እግዚአብሔር ከሰጠው ተስፋ አንድም ያልጎደለ መሆኑን በመጥቀስ፣ አንባቢዎቹ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ማለትም፣ ምድር እንደሚሰጠው፣ ህዝብ እንደሚያደርገው እና ከህዝቡም ጋር እንደሚኖር የተናገረውን እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል፡፡ ከዚያም ምድሪቱ በሙላት ስትከፋፈል፣ ከዘፍጥረት 12 ጀምሮ፣ ከረጅም ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ለአብርሃም በሰጠው ተስፋ መሠረት እስራኤል በምድሪቱ ላይ ሰፍራ እናያታለን፡፡

ሬቨረንድ ሚካኤል ጄ.ግሎዶ

## ይሁዳ

በእነዚህ የመጽሐፉ መደምደሚያዎች መካከል አራት ዋና ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ የመጀመሪያውም በ 14፡6 – 15፡63 የሚገኘውና ከእስራኤል እውቅ ነገዶች አንዱ የሆነው ይሁዳ የተጠቀሰበት ነው፡፡ እንደ እነዚህ ጥቅሶች አገላለጥ፣ ይሁዳ የደረሰው እጅግ ሰፊ ርስት ሲሆን፣ ይህም በስተ ደቡብ እስከ ኔጌቭ ከዚያም እስከ ኤዶም ድንበር የሚዘልቅ ነው፡፡ በስተ ምዕራብ ደግሞ፣ እስከ ፍልስጤኤማውያን ምድር ይዘልቅና የሜድትራኒያንን ወደብ ዳርቻ በመያዝ እስከ ግብፅ ድንበር ይስፋፋል፡፡ በስተ ሰሜን ደግሞ የኢየሩሳሌምን ሰሜናዊ ዳርቻ በመታከክ ወደ ሜድትራኒያን ዳርቻ ድረስ ይዘልቃል፡፡ ወይም በዚያን ዘመን አጠራሩ ወደ ኢያቡስ ይደርሳል፡፡ በስተ ምሥራቅ ደግሞ እስከ ሙት ባህር ድረስ ይደርሳል፡፡

ጸሐፊው የይሁዳን የርስት ድልድል ዝርዝር ለምን በመጀመሪያ ላይ ለምን እንዳመጣውና ይሁዳ ምን ያህል ርስት እንደወረሰ አስምሮበት ለምን እንደተረከ ለመረዳት አያስቸግርም፡፡ በዘፍጥረት 49፡8-12 አገላለጽ፣ ይሁዳ የእስራኤል የንግሥና የዘር ሐረግ ያለው ነገድ ነው፡፡ ጸሐፊአችንም ለይሁዳ ነገድ በተሰጠው አክብሮት ላይ አስምሮበታል፡፡ ይህንንም ደረገው ከይሁዳ ነገድ ለሆነው ብርቱ ተዋጊ፣ ለካሌብ የተሰጠውን ርስት ዝርዝር በማስቀደም የትረካው መጀመሪያ በማድረግ ነው፡፡ ከዚያም በማስከተል፣ ለሌሎቹ ነገዶች ካደረገው እጅግ ሰፋ ባለ መንገድ በይሁዳ ግዛት ውስጥ የሚገኙትን 126 ከተማዎችና መንደሮ በስማቸው እየጠቀሰ ዘርዝሯቸዋል፡፡

## ኤፍሬምና ምናሴ

ከዮርዳኖስ መለስ ለይሁዳ የተሰጠውን የርስት ድልድል ዘገባ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ቀጣዩን ሰፋ ያለ ዘገባ እናገኛለን ያም በምዕራፍ 16 እና 17 ላይ የሚገኘውና የዮሴፍ ልጆች ለሆኑት ለኤፍሬምና ለምናሴ ነገዶች የተሰጠው ሁለተኛው ሰፋ ያለ ድልድል ነው፡፡

ኤፍሬምና ምናሴ በከነዓን ምድር ሴሜናዊ ግዛት ውስጥ ሰፋ ያለ ርስት ተቀብለዋል፡፡ ርስታቸውም ከዮርዳኖስ ወንዝ አንስቶ እስከ ሜዲትራኒያን ባህር ድረስ የሚዘልቅ ሆኖ፣ ኤፍሬም ከምናሴ በስተ ደቡብ በኩል ሰፍሯል፡፡ እነዚህ ድንበሮች ከጠቅላላው የተስፋዪቱ ምድር ድንበሮ ሁሉ እጅግ ለም የሆኑት ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ በኩል ያለው ምድር ለምናሴ ነገድ እኩሌታ እንደተሰጠ ታስተውላላችሁ፡፡

እነዚህ ነገዶች በእስራኤል የርስት ክፍፍል ውስጥ እንዲህ ሰፋ ያለ ድርሻ ማግኘታቸው ምን ያህል የተከበሩ እንደሆኑ የሚያሳይ መሆኑ አያስደንቅም፡፡ ዮሴፍ በግብጽ ምድር ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ በመኖሩ እጅግ በጣም የተከበረ ሰው እንደነበረ እናውቃለን፡፡ የያዕቆብ የበኩር ልጅ የሆነውን የሮቤልን ብኩርና ተካ ስለዚህም የበኩር ልጅን እጥፍ ርስት በሁለቱ ልጆቹ አማካይነት ተቀበለ፡፡

> ***እንግዲህ፣ ኤፍሬምና ምናሴ የዮሴፍ ልጆች ናቸው፡፡ የያዕቆብ ልጆች አይደሉም፡፡ ያዕቆብ ስሙ ተለውጦለት እስራኤል የተባለና ዐሥራ ሁለት ልጆች የነበሩት ሰው ነው ያዕቆብ፡፡ ከእነርሱ አንዱ ዮሴፍ፣ ወደ ግብጽ ለባርነት ተሸጠ፡፡ ደግሞም በመቀጠል ሌላኛው ልጅ፣ ሌዊ፣ ደግሞ ከዐሥራ ሁለቱ ነገዶች ጋር አልተቆጠረም ይህም የሆነው እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የበኩር ልጆች ወክሎ የእርሱ ርስት እንዲሆንለት የሌዊን ነገድ በመምረጡ ነው፡፡ ከዚያም ወደ ያዕቆብ በረከት ስንመጣ፣ ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች ይባርካቸዋል፡፡ በኤፍሬምና በምናሴም ላይ የባርኮት ቃሎቹን ይናገራል፣ ያም ሲሆን ሁለቱ ልጆቹ በሌዊና በዮሴፍ ፈንታ ተቆጠሩ ማለት ነው፡፡ ከዚያም ምድሪቱን በሚከፋፈሉበት ወቅት፣ ዐሥራሁለቱ ነገዶች ርስታቸውን ሲደላደሉ፣ ኤፍሬምና ምናሴ እያንዳንዳቸው ለየነገዱ በተደረገው ድልድል መሠረት ርስት ይደርሳቸዋል፡፡ እናም ዮሴፍ፣ በልጆቹ፣ በኤፍሬምና በምናሴ ተወከለ ማለት ነው፡፡***
>
> – ***ዶ/ር ጀምስ ኤም. ሃሚልተን***

ምዕራፍ 16 የሚጀምረው ከዮርዳኖስ መለስ ለዮሴፍ ስለተሰጠው ምድር መጠነኛ መግለጫ በመስጠት ሲሆን፣ ከዚያ በመቀጠል ስለ ኤፍሬም ነገድ ለየት ያለ ዝርዝር ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ከዚህም በማስከተል፣ በምዕራፍ 17 ውስጥ፣ ትረካው ወደ ምናሴ ነገድ ይሸጋገርና በዘሁልቁ 27 የተጠቀሰውን የሰለጵዓድ ሴት ልጆ ርስት ድልድል ታሪክ በማካተት ይዘግባል፡፡

ይህ ክፍል የሚጠናቀቀው ኤፍሬምና ምናሴ ካላቸው በርካታ ቁጥር የተነሳ እንዴት ሰፊ ርስት ሊሰጣቸው እንደቻለ ኢያሱ የሰጠውን ማብራሪያ በማስፈር ነው፡፡

ለኤፍሬምና ነምናሴ ነገዶች የተሰጠው የቀዳሚነት ስፍረ እጅግ አገራሚ ነው ምክንያቱም እነዚህ ነገዶች መጽሐፋችን በተጻፈበት ወቅት ለተፈጠሩ ችግሮች ሁሉ መንስዔዎች ስለነበሩ ነው፡፡ ጸሐፊአችን ግን፣ ታሪኩ ይህንን ቢመስልም፣ እግዚአብሔር የዮሴፍን ነገዶች እንዴት እንዳከበራቸው እስራኤል እውቅና ሊሰጥ እንደሚገባ ማመልከት በመፈለጉ እንዲህ አስፍሮታል፡፡

## ትናንሽ ነገዶች

ታላላቅ በሆኑት በይሁዳ፣ በኤፍሬምና በምናሴ ነገዶች የርስት ልድል ላይ ተኮረው ዘገባ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ጸሐፊአችን በምእራፍ 18 እና 19 ውስጥ ወዳሰፈራቸው ወደ ትናንሾቹ ነገዶች ይሸጋገራል፡፡ ሲጀምርም በ18፡1-10 በተጠቀሰውና ኢያሱ ከእያንዳንዱ ነገድ ተወካዮችን ጠርቶ ምድሪቱን እንዲሰልሉ በሰጠው መመሪያ ይጀምራል፡፡ ከዚያም በምዕራፍ 19፡45-51 ባለው ታሪክ ማለትም ነገዶቹ የርስት ክፍፍሎቹን ማጽደቃቸውን በመጥቀስ ይደመድማል፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የጠቀሰው ለኢያሱ ለራሱ ለየት ያለ ቤተሰባዊ ርስት ስለደለደሉለት ነው፡፡

በእነዚህ የመክፈቻና የመዝጊያ ትረካዎች መካከል፣ ጸሐፊአችን ለእስራኤል ትንንሽ ነገዶች ማለትም፣ ለብንያም፣ ለስምዖን፣ ለዛብሎን፣ ለይሳኮር፣ ለአሴር፣ ለንፍታሌም እና ለዳን የተሰጠውን የርስት ክፍፍል ዘግቦልናል፡፡ እነዚህ ነገዶች ርስት የደረሳቸው ቢሆንም፣ የይሁዳን፣ የኤፍሬምንና የምናሴን ነገዶች ያህል አልደረሳቸውም፡፡ ቆየት ካሉ ዘመናት በኋላም፣ ትንንሾቹ ነገዶች ምድሮቻቸውን አስከብረው የማቆየት ፈተና ገጥሟቸዋል፡፡ ጸሐፊአችን ራሱ በ19፡9 ውስጥ የስምዖን ነገድ ርስት “በይሁዳ ነገድ ርስት መካከል ውስጥ” እንደሚገኝ አመልክቷል፡፡ ይህም ስምዖን ነገድ በይሁዳ ነገድ የተዋጠ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በ19፡47 ውስጥ ደግሞ “የዳን ነገድ ድንበር የጠፋባቸው” መሆኑን አመልክቷል፡፡ ታሪኩንም በመሳፍንት 18 ውስጥ እናነብበዋለን፡፡ እነዚህና ሌሎችም አለመረጋጋቶች ትናንሾቹን ነገዶች እንዳስቸገሯው በመገንዘብ፣ ተደራሲያኑ እነዚህን የርስት ድልድሎች እውቅና እንዲሰጧቸው ለማድረግ ጽፎላቸዋል፡፡

## ሌዋ

ከዮርዳኖስ መለስ ኢያሱ ያደረገው የርስት ድልድል በምዕራፍ 20 እና 21 ውስጥ ተመዝግቦ የምናገኘውን የሌዊን ነገድ ድርሻም አካቷል፡፡ ጸሐፊአችን ስለ ሌዊ ነገድ ያቀረበውን ዘገባ የጀመረው በ20፡1-9 ላይ ባሰፈረው የመማፀኛ ከተሞችን ስም በማውጣት ነው፡፡ ዘጸዓት 21፡12-14 እና ዘዳግም 19፡1-13 ላይ በሰፈረው ዘገባ መሠረት ሆን ብለው ሳይሆን ሳያውቁ ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች የእስራኤል ፍርድ ቤቶች የወንጀላቸውን ሁኔታ አጣርተው በደለኛና ንፁህ እስከሚሏቸው ድረስ መማፀኛ እንዲሆኑ ታስበው የተቋቋሙ ናቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠልም፣ ጸሐፊአችን በምዕራፍ 21 ውስጥ የሌዋውያንን ከተሞች ዝርዝር አስፍሯል፡፡ ይህም ሙሴ በዘኁልቁ 35፡6-34 የሰጠውን መመሪያ የተከተለ ነው፡፡

የመማፀኛ ከተሞችና ሌሎቹ የሌዋውያን ከተሞች በእስራኤል ምድር ውስጥ በሚገኙ በሌሎቹ ነገዶች ድንበሮች ውስጥ ተሰበጣጥረው ነው የሚገኙት፡፡ ይህ ሌዋውያን እያንዳንዱን ነገድ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለማዘጋጀት እድል ይሰጣቸዋል፡፡ የሚያሳዝነው ግን፣ እነዚህ ድልድሎች ተግዳሮት በሚመጣ ወቅት የሚረሱ መሆናቸው ነው፡፡ ሆኖም የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ የሌዋውያን አገልግሎት ለህገሪቱ ደህንነት እጅግ ወሳኝ ሚና እንዳለው እንዲገነዘቡ ተደራሲያኑን በጽኑ ያሳስባቸዋል፡፡

ለየት ያሉትን የነገዶች የርስት ክፍፍል አወቃቀርና ይዘት በልቡናችን በመያዝ፣ የእነዚህን ምዕራፎች ቀደምት ትርጓሜ በአጭሩ ወደመመልከቱ እንሸጋገር፡፡

## ቀደምት ትርጓሜ

በእኛ ዘመን የምንገኝ ተደራሲያን የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ያሰፈራቸውን መልክዓ-ምድራዊ ዝርዝሮች በመደነቅ የመመልከት ችግሮች በተደጋጋሚ ይስተዋልብናል፡፡ እርሱ የሚያቀርበው ጥሪ ግን እራኤላውያን

በመጀመሪያ የተሰጣቸውን ብሔራዊ ድንበር እንዲያስከብሩ ብቻ አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ነገድ የሰጠውን ርስት ለይተው እንዲያውቁና ልዩነቶቹንም እንዲያስተውሉ በማድረግ በዚያም መሠረት የእግዚአብሔርን መንግሥት የማስፋፋቱን ሥራ እንዲገፉበት ለማነሳሳትም ነው፡፡

ጸሐፊአችን የተለመደውን የአጻጻፍ ስልቱን በመከተል፣ የእስራኤልን ነገዶች ለየት ያለ የርስት ክፍፍል ሲያሰፍር አምስት መሪ ሃሳቦችን አያይዞ ያቀርብልናል፡፡

## መለኮታዊ ሥልጣን

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ለነገዶቹ የተደረገውን የርስት ድልድል የመራ መለኮታዊ ሥልጣን እንዳለ አጽንዖት ሰጥቶታል፡፡ ከዮርዳኖስ ማዶ ስለነበረው የርስት ድልድል ጸሐፊአችን ሲዘግብ አራት ጊዜ ማለትም በ13፡8፣ 15፣24 እና 29 ውስጥ አጽንዖት ሰጥቶ አስፍሮታል፡፡ እነዚያም በእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥልጣን የተሰጣቸው መሪ ሙሴ ስለ ሰጣቸው የርስት ድልድል የሚያወሱ ናቸው፡፡

ጸሐፊአችን በተጨማሪም ከዮርዳኖስ መለስ ካሉት የነገዶች የርስት ክፍፍሎች ጀርባ ስላለው መለኮታዊ ሥልጣንም አመልክቷል፡፡ በዚህ የመግቢያ ማጠቃለያ በ14፡1 ላይ፣ "ካህኑ ኤሊዔዘር፣ የነዌ ልጅ ኢያሱ እና የየነገዶቹ አለቆች" ምድሪቱን አደላደሉ በማለት ጽፏል፡፡ በ17፡4 ውስጥ ስለ ኤፍሬምና ስለ ምናሴም ሲዘግብ ተመሳሳይ ነጥብ አስቀምጧል፡፡ በድጋሚም በ19፡51 ውስጥ ስለ ትናንሾቹ ነገዶች ሲዘግብና በ21፡1 ላይ ስለ ሌዊ ነገድ ሲያወሳም ይህንኑ ሃሳብ አስፍሯል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ ጸሐፊአችን በ20፡1 ውስጥ በተለመደው የአመዘጋገብ መንገድ፣ "ከዚያም ጌታ ኢያሱን እንዲህ አለው… " በማለት የሌዊን ነገድ የርስት ድልድል አስተዋውቋል፡፡ እንድምታዎቹም ለመጀመሪያዎቹ ተደራሲያን በጣም ግልጽ ነበሩ፡፡ በእነዚህ ለየት ያሉ የነገዶች ርስት ክፍፍል ያልረኩ ካሉ ልረኩት በእግዚአብሔር አመራር በተከናወነው ድልድል እንደሆነ ይቆጠርባቸዋል፡፡

## የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን

በሁለተኛ ደረጃ፣ የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ ለየት ስላለው የእስራኤል ነገዶች የርስት ድልድል ያወሳል፣ እነዚህም ክፍፍሎች በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ እንደሆነም አጽንዖት ሰጥቶ ይዘግባል፡፡ ጸሐፊአችን ለእያንዳንዱ ነገድ የተሰጠውን መሬት ድርሻ "ርስት" በማለት ደጋግሞ ሲጠቅስ የተጠቀመው *nachalah* (נַחֲלָה.) የተሰኘውን የዕብራይስጥ ቃል ነው፡፡ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው፣ ይህ ቃል በቀጥታ የሚገናኘው እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከሙሴ ጋር ከገባው ቃል ኪዳን ጋር ነው፡፡ በ13፡32 ውስጥ፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉትን ምድሮች "ርስቶች" ብሎ ጠርቷቸዋል፡፡ በቁጥር 33 ውስጥ ደግሞ፣ የሌዋውያንን ልዩ ድርሻ "ርስታቸው" በማለት ጠቅሶታል፡፡ ከዮርዳኖስ መለስ ስላሉት የርስት ክፍፍሎች በሚያወሳበት ክፍል መግቢያ ላይ ርስት የሚለውን ቃል በ14፡1፣2፣እና 3 ላይም ጠቅሶታል፡፡ የይሁዳንም ድርሻ በተመሳሳይ መንገድ ርስት በማለት በ14፡9፣ 13 እና 15፡20 ላይም ጠቅሶታል፡፡ በ16፡4 እና በተጨማሪ ሰባት ጊዜያት የኤፍሬምንና የምናሴንም በተመሳሳይ መንገድ ጠቅሶታል፡፡ የትናንሾቹን ነገዶች ድልድልም ወደ ዐሥራ ሰባት ለሚያህል ጊዜ ርስት በማለት ጠቅሶታል፡፡ በ21፡3 በመጨረሻው ክፍል ውስጥ ስለ ሌዊ ነገድ ሲጠቅስ፣ እያንዳንዱ ነገድ እንዴት አድርጎ ከየርስታቸው የከብቶች ማሰማሪያ ስፍራና ለከተሞች የሚሆንን ስፍራ እንዴት መስጠት እንዳለበት ተናግሯል፡፡ በመጨረሻም፣ የዚህን ክፍል ማጠቃለያ ባሰፈረበት በ21፡43 ውስጥ፣ "እግዚአብሔርም ይሰጣቸው ዘንድ ለአባቶቻቸው የማለላቸውን ምድር ሁሉ" ለእስራኤላውያን ሰጣቸው በማለት ጸሐፊአችን ጽፏል፡፡ እነዚህ ሁሉ ማጠቀሻዎች በግልጽ እንዳስቀመጡልን እነዚህ ለየት ያሉ የየነገዶቹ የርስት ክፍፍሎች በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን እናረጋግጣለን፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው እነዚያን ቸል ቢል፣ እግዚአብሔር እንደ ቃል ኪዳን አምላካቸው የገባላቸውን የተቀደሱ ተስፋዎች ቸል ማለታቸውም ጭምር ነው፡፡

## የሙሴ ህግ ስነ-ልክ

በሦስተኛ ደረጃ፣ በዚህ ለእስራኤል ልጆች በተሰጠው ለየት ያለ የርስት ዘገባው ውስጥ፣ የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ በተጨማሪም በሙሴ ህግ ላይ ለተቀመጠው ስነ-ልክ መታዘዝ ወሳኝ መሆኑንም አመልክቷል፡፡ ይህ አጽንዖቱ ከዮርዳኖስ መለስ ለውን በዘገበበት ክፍል ላይ በግልጽ ታይቷል፡፡ የመግቢያ ማጠቃለያው ላይ፣ ማለትም በ14፡2 ውስጥ ኢያሱ ተግባራዊ ያደረገው፣ "እግዚአብሔር በሙሴ እጅ እንዳዘዘ" እንደሆነ ጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም፣ በ14፡5 ውስጥ፣ "እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘ" እስራኤላውያን ምድሪቷን ተከፋፈሉ ብሏል፡፡ በ17፡4 ውስጥ ደግሞ፣ የሰለጰዓድ ሴት ልጆችም "እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳዘዘው እንዲሰጣቸው" ጠይቀዋል፡፡ በ20፡2 ላይ የተዘገበው የሌዋውያን ታሪክ እንደሚያሳየን እግዚብሔር "በሙሴ የተናገረውን" እስራኤላውያን ሊጠብቁ እንደሚገባቸው አመልክቷል፡፡ ደግሞም፣ በ21፡2፣8 በሚገኘው በመዝጊያው ማጠቃለያ መሠረት፣ "እግዚአብሔርም በሙሴ እጅ እንዳዘዘ" ከተሞች ለሌዋውያን ሊለዩላቸው ይገባል፡፡

ጸሐፊአችን በእነዚህ ምዕራፎች የሙሴን ህግ ስነ ልክ ሲጠቅስ ማመልከት የፈለገው በየትኛውም ዘመን የሚመጡ የእስራኤል ትውልዶች እነዚህን የምድር ክፍፍሎች ሊጠብቁ እንደሚገባ ነው፡፡ እነርሱን መተላለፍ ማለት በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ መርገምን ማምጣት ነው፡፡ እነርሱን ማክበር ደግሞ በረከቱን ማምጣት ነው፡፡

## የእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል

በአራተኛ ደረጃ፣ እነዚህ ለየት ያሉ የነገዶች የርስት ክፍፍሎች በእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል የተረጋገጡ መሆናቸውን እነዚህ ምእራፎች እውቅና ይሰጣሉ፡፡ ከዮርዳስ ማዶ ያሉ ምድሮች ክፍፍል የተጠቀሰበት 13፡10፣27 የሴዎንን ንጉሥ ተዓምራዊ ሽንፈት ይጠቅሳል፡፡ በ13፡22 ውስጥ ስለ በለዓም መገደል የምናነብብ ሲሆን፣ በ13፡31 ደግሞ በባሳን በአግ ላይ ስለተገኘው ድል እናነብባለን፡፡ እነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች የሚያስገነዝቡን ከዮርዳኖስ ማዶ እግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ሥራውን እየሠራ መሆኑን ነው፡፡

በተጨማሪም፣ ከዮርዳኖስ መለስ በተደረጉት የርስት ክፍፍሎችም ውስጥ ዕጣን በመጣል አማካይነት እግዚአብሔር በልዕለ ተፈጥሮአዊ አሠራሩ ጣልቃ ይገባ እንደነበር ጸሐፊአችን ዘግቧል፡፡ ዘኍልቁ 36፡2 እና ምሳሌ 16፡33 የመሳሰሉት ክፍሎች፣ ዕጣ መጣል እግዚአብሔር ለእስራኤል ፈቃዱን ከሚገልጥባቸው ልዕለ ተፈጥሮአዊ መንገዶች አንዱ መሆኑን ያብራራሉ፡፡ ከዮርዳኖስ መለስ ያለው የርስት ክፍፍል መግቢያ ዕጣ መጣልን በ14፡2 ውስጥ ይጠቅሰዋል፡፡ ለትናንሽ ነገዶች በተደረገው የርስት ክፍፍልም ውስጥ ዕጣ መጣል ዐሥራ አንድ ያህል ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ እስራኤላውያንም ለሌዊ ነገድ ርስትን ሲደለድሉ ዕጣ መጣላቸውን በ21፡4 እና 10 ውስጥ እናገኛለን፡፡

ጸሐፊአችን ደግሞ ደጋግሞ የእግዚአብሔርን ልዕለ ተፈጥሮአዊ ተሳትፎ የጠቀሰበትን ዓላማ መገንዘብ አዳጋች አይሆንም፡፡ ከቀደምት ተደራሲያኑ መካከል ከነበሩ ሰዎች አንዳንዶቹ ከእነዚህ ከነገዶች የርስት ክፍፍሎች ወጣ የማለት ፈተና ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ጸሐፊአችን ግን ደግሞ ደጋግሞ የሚያሳስበው እነዚህ ክፍፍሎች በእግዚአብሔር በራሱ የተደነገጉ ስለሆነ በፍጹም ሊጣሱ እንደማይገባ ነው፡፡

> በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ ማን የትኛው ምድር እንደደረሰው ለመወሰን ዕጣ መጣሉን ተመዝግቦ ማገበባችን ማራኪ ነው፣ ምክንያቱም እኔ እንደማስበው ጉዳዩ በእግዚአብሔር እጅ ነው ማለት ነው፡፡ ምንም እንኳን ኢያሱ ማን ምን ሊያገኝ እንደሚገባ ቢመርጥም፣ ይህንን ለእነርሱ የሰጠ ግን እግዚአብሔር በመሆኑ መበላለጥ ሊኖር አይችልም፡፡ በተጨማሪም ዕጣ መጣሉ፣ አንድ ወሳኝ የሆነን ነገር ያመለክተናል፣ ያም ጉዳዩ የእግዚአብሔርና የህዝቡ መሆኑን ሲሆን፣ እግዚአብሔርም ለህዝቡ የሚሰጠው ያለ አድልዎ ነው የሚለውን ያጸናል፡፡ እኔ እንደማስበው፣ ሰው ሁሉ ሊረዳው የሚገባው ነገር፣ እግዚአብሔር የህዝቡን የንብረት ባለቤትነት ጥቅም የሚያስከብር መሆኑን፣ ለእነርሱ ደግሞ የርስት ጉዳይ እጅግ ወሳኝ መሆኑን ነው፡፡ ደግሞም ማራኪ የሆነው ነገር መሬቱ ለማንም የማይላለፍ መሆኑ ነው፡፡ ማንም ቢሆን ከርስቱ ለዘላለም ተነቅሎ አይቀርም፡፡ ምናልባት እንኳን ምድራቸውን ቢሸጡም፣ ምድሩ ወደ እነርሱ የሚመለስበት የኢዮቤልዩ ዓመት አለ፡፡ እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በአንድነት ተያይዞ የሚያሳዩን ይህ ርስት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ርስት፣ ከእግዚአብሄር የተሰጣቸው መብታቸው ስለሆነ እግዚአብሔር

ድንበራቸውን ያስከብራል፣ ማንም ቢሆን፣ ማለትም ንጉሥም እንኳን ቢሆን፣ ወደ እነርሱ መጥቶ "ይህ የእናንተ ምድር አይደለም" ሊላቸው አይችልም፡፡ ነገሥታት ሞክረዋል፣ ግን ህጋዊ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ለእነርሱ የሰጣቸው ስጦታ ስለሆነና እግዚአብሔር እንደራሱ ህዝብ የሰጣቸው ርስት በመሆኑ ነገሥታት ያንን የማድረግ መብት የላቸውም፡፡

- **ዶ/ር ቲ.ጄ. ቤትስ**

## እስራኤል በጠቅላላ

በአምስተኛ ደረጃ፣ በመጽሐፉ ውስጥ ቀደም ብለን እንዳየናቸው ምዕራፎች ሁሉ፣ እነዚህም በእስራኤል ለየት ያሉ የነገዶ የርስት ክፍፍል የሰፈረባቸው ምዕራፎችም እስራኤልን በጠቅላላ የሚያካትት መሆኑን እናስተውላለን፡፡ ይህ ክፍል አጽንዖት ያደረገበት ጉዳይ ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉት ምድሮች እንዴት ለእያንዳንዱ ነገድ ማለትም ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ እንደተከፋፈሉ በሚዘግብ መንገድ የሰፈረ መሆኑን እናያለን፡፡ ከዮርዳኖስ ወዲህ ያለውም የርስት ክፍፍል ተመሳሳይ መንገድ ይከተላል፡፡ የሚዘግበው ለይሁዳ፣ ለኤፍሬምና ለምናሴ ስለተሰጡት ምድሮች ብቻ ሳሆን ለትናንሾቹ ነገዶችም የተደለደሉትን ያካትታል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ለሌዊ ነገድ የተሰጡ ከተሞችንም ለየት አድርጎ ዘግቧል፡፡

ጸሐፊአችን በእስራኤል ነገዶች ሁሉ ላይ ያቀረበው ዝርዝር ዘገባ የሚያመለክተን እስራኤል በጠቅላላ በተስፋዪቱ ምድር ውስጥ ሊኖሩ ይገባቸዋል የሚለውን እምነቱን ነው፡፡ መጽሐፉችን በተጻፈበት ዘመን፣ አንዳንድ ነገዶች በሌሎች ውስጥ የተዋጡ ነበሩ፡፡ ሌሎቹ ነገዶች ደግሞ እዚህም እዚያም ድንበሮቻቸውን በጠላቶቻቸው አስደፍረው ነበር፡፡ እናም አሦራውያን ሰሜናዊውን የእስራኤልን መንግሥት ሲደመስሱ እና ባቢሎናውያን ይሁዳን ድል ሲያደርጉ በርስታቸው ላይ ቀርተው የነበሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ ቅሬታዎች የሆኑት ጥቂቶቹ ብቻ ነበሩ፡፡ ጸሐፊአችን ግን የሚያበረታታው እያንዳንዱ እስራኤላዊ ለዚህ የተከበረ እውነት ራሳቸውን እንዲሰጡ ነው፡፡ እስራኤል በጠቅላላ በተስፋዪቱ ምድር ውስጥ የተገባውን ርስት ሊያስከብር ይገባዋል፡፡

የኢያሱ መጽሐፍ ለእያንዳንዱ ነገድ በግል የተሰጠውን የርስት ክፍፍል መሠረት በማድረግ ከመጀመሪያው የነበራቸውን የድንበር ወሰን በመዘርዘር የእስራኤላውያንን ጠቅላላ የየነገዶች ውርስ እንዴት እንደዘገበው ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ በትምህርታችን ሂደት በቀጣዩ እርከን ላይ ወደምናነሳው ሦስተኛ ርዕሳችን ማለትም የእስራኤል ብሔራዊ አንድነት እንሸጋገር፡፡

# ብሔራዊ አንድነት

ለበርካታ ምዕተ ዓመታት የእስራኤል ነገዶች በመከፋፈል አንዳቸው በሌላቸው ላይ ደግመው ደጋግመው ይነሱ እንደነበር እናስተውላለን፡፡ ነገር ግን እስራኤላውያን አንድ በመሆን እንደ አንድ ህዝብ ካልቆሙ በስተቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት በማስፋፋቱ ረገድ ወደፊት ሊገፉ እንደማይችሉ ጸሐፊአችን ያውቅ ነበር፡፡ ይህንን ጉዳይ በትክክል ለማስረዳት፣ ጸሐፊአችን ይህኛውን ክፍል የደመደመው በኢያሱ ዘመን የእስራኤልን አንድነት በሚፈታተን መንገድ የተከሰተውን ፈታኝ ግጭት በማንሳት ነበር፡፡

ደግመን ደጋግመን እንደተመለከትነው፣ ጸሐፊአችን ደጋግሞ ትኩረት ያደርግ የነበረው ተፈጥሮአዊ በሆኑትና ከዮርዳኖስ ማዶና ከዮርዳኖስ መለስ በነበሩት የእስራኤል ነገዶች ክፍፍል ላይ ነው፡፡ በኢያሱ ዘመን መልክዓምድራዊው ክፍፍል ችግር ፈጣሪ ነበር ምክንያቱም በዮርዳኖስ ማዶና ማዶ ባሉ ነገዶቸ መካከል ወደ ጦርነት ሊያስገባ የሚችል ግጭት ይቀሰቅስ ስለነበር ነው፡፡ ስለዚህም፣ ጸሐፊአችን በእስራኤል ነገዶች ላይ ያቀረበውን ዘገባ ሁለተኛውን ክፍል ሲደመድም ኢያሱ ከዮርዳኖስ ማዶና መለስ ያሉ ነገዶች እንዴት አንድነታቸውን ሊጠብቁ እንደሚገባ ያከናወነውን ድርጊት መለስ አድርጎ በማሳሰብ ነበር፡፡ እነዚህም ወቅቶች የሚያሳስቡት ምንድነው ብንል፣ ቀደምት ተደራሲያኑም በዘመናቸው ተመሳሳይ ውጥረት ቢገጥማቸው እንዴት ሊያስወግዱት እንደሚገባ ማመልከት ነው፡፡

የእስራኤልን ብሔራዊ አንድነት ስንመለከትም ተመሳሳዩን ንድፋችንን በመከተል በመጀመሪያ የዚህን ክፍል አወቃቀርና ይዘት እንመረምራለን፣ ከዚያ ደግሞ ቀደምት ትርጓሜውን እንዳስሳለን፡፡ አስቀድመን የዚህን ምዕራፍ አወቃቀርና ይዘት እንመልከት፡፡

## አወቃቀርና ይዘት

በምዕራፍ 22 ውስጥ የምናገኘው ስለ እስራኤል ብሔራዊ አንድነት የሚያወሳው ክፍል ቀጥተኛ ትረካ ሲሆን አምስት ዋና እርከኖችን በቅደም ተከተል የሚዘረዝር ነው፡፡ የሚጀምረውም ከቆጥር 1-10 በሚገኘውና ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉ ነገዶች በተከሉት መሠዊያ ችግር ድራማዊ ገጽታ ነው፡፡

### የመሰዊያ ግንባታ

ከዮርዳኖስ መለስ ያሉትን ርስቶች እስራኤል ድል አድርጋ ከያዘች በኋላ፣ ኢያሱ የሮቤልን፣ የጋድንና የምናሴን ነገድ እኩሌታ ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ ወደሚገኘው ርስታቸው እንዲሄዱ አድርጓል፡፡ ለእግዚአብሔር በመታመን እንዲዘልቁም አስጠንቅቋቸዋል፡፡ ኬርኖኖስ ማዶ ያሉ ነገዶች ግን፣ በመንገዳቸው ላይ ሳሉ፣ ከዮርዳኖስ ወንዝ አቅራቢያ አስቸጋሪ የሆነ ግዙፍ መሠዊ ሠሩ፡፡ ከዮርዳኖስ መለሰ ያሉ ነገዶችም ይህንን ሲሰሙ፣ መሠዊያው የቆመው በሙሴ የመገናኛ ድንኳን ውስጥ የሚገኘው የእግዚአብሔር መሠዊያ ምትክ እንደሆነ አድርገው አሰቡ፡፡

### የጦርነት ጥንስስ

ከቁጥር 11 -14 ያለው ክፍል የጦርነት እሳት ሊለኮስ በሚችልበት ስጋት የተሞላ ትረካን የያዘ ክፍል ነው፡፡ ምክንያቱም ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉ ነገዶች በተከሉት መሰዊያ ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ እንዳይመጣ ስለፈሩ ሲሆን፣ ከዮርዳኖስ መለስ ያሉ ነገዶች ሊያጠቁዋቸው እቅድ አወጡ፡፡ ሆኖም፣ ጦርነቱን ለማስቀረት ሲሉና ከዮርዳስ ማዶ ያሉ ነገዶችን ለመሞገት ሲሉ፣ የዓልዓዛርን ልጅ፣ ፊንሐስን እና ዐሥር የነገድ አለቆችን አስቀድመው ላኩ፡፡

### ሙግት

ከቁጥር 15-21 የሚገኘውና ረዘም ያለው የታሪካችን አቅጣጫ ለወጥ ያለበት ክፍል፣ በልዑካን ቡድኑና በዮርዳኖስ ማዶ ባሉ ነገዶቸ መካከል የተደረገውን ሙግት የሚዘግብ ነው፡፡ ይህ አዲስ የተተከለው መሠዊያ መስዋዕት ሊቀርብ የሚገባው በመገናኛው ድንኳን ብቻ እንደሆነ የሚደነግገውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚተላለፍ እንደሆነ ልዑካኑ አስጠንቅቀዋል፡፡ ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉ የነገድ አለቆች ግን በከፍተኛ ግለት መሠዊያውን ያቆሙት ለመስዋዕት እንዳልሆነ ማብራሪያ ሰጡ፡፡ ይልቁኑ መሠዊውን ያቆሙት ከተቀሩት ነገዶቸ ጋር ያላቸውን አንድነት ለማሳየት እንደሆነና ይህንንም ያደረጉት የተቀሩት ነገዶች እነርሱን ከመንግስታቸው ውጪ እነዳያደርጓቸወ ስለፈሩ ነበር፡፡ በምላሹም፣ ልዑካኑ ደስ አላቸው ምክንያቱም ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉ ነገዶች ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት እንዳላጓደሉ በማወቃቸው ነው፡፡

### የጦርነቱ ጥንስስ መምከን

በቁጥር 32 እና 33 ላይ የተዘገበውና የጦርነቱ ጥንስስ ስለ መምከኑ የሚያወሳው ትረካ የተወሰደውን እርምጃ ይዘረዝራል፡፡ የልዑካኑ ቡድን የተረዱትን ነገር ሲያስረዱ፣ ከዮርዳኖስ መለስ ይኖሩ የነበሩት ነገዶች እግዚአብሔርን በማመስገን ስለ ጦርነት ያደርጉ የነበረውንም ምክክር አቋረጡት፡፡

### የመሠዊያው ስያሜ

ይህ ድራማዊ ውጥረት የረገበበት የመጨረሻው ታሪክ የሚገኘው በቁጥር 34 ውስጥ ሲሆን ያም ስለ መሰዊያው ስያሜ የሚያወሳው ታሪክ ነው፡፡ ከዮርዳኖስ ማዶ የሚገኙት ነገዶች መሠዊያውን የሠሩበትን ዓላማ የገለጡት መሠዊያውን “ምስክር” የሚል ስያሜ በመስጠት ነው፡፡ ማብራሪያ ሲሰጡም፣ “እግዚአብሔር አምላክ ለመሆኑ ይህ በመካከላችን ምስክር

ነው” አሉ፡፡ ይህንንም በማድረጋቸው፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉ ነገዶች የዓላማቸውን ክቡርነት ያረጋገጡ ሲሆን መሠዊውን የተከሉበት ዋና ዓላማ ከእስራኤል ጋር ያላቸውን አንድነት ለማረጋገጥ መሆኑን አሳይተዋል፡፡

ይህንን ስለ እስራኤል አንድነት የሚያወሳውን ትረካ አወቃቀርና ይዘት በልቡናችን አድርገን፣ ስለ ቀደምት ትርጓሜው ጥቂት ሃሳቦችን ወደ መሰንዘሩ እንሸጋገር፡፡

# ቀደምት ትርጓሜ

ጸሐፊአችን የመጽሐፉን ይህኛውን ክፍል በምዕራፍ 22 ላይ ባሰፈረው ትረካ ለምን እዳጠናቀቀው መገንዘብ አዳጋች አይሆንም፡፡ ይህ ታሪክ የሚያብራራልን ምንም እንኳን ነገዶች ወደ እርስ በርስ ፍልሚያ ሊያስገባቸው በሚችል ግጭት አፋፍ ላይ ቢገኙም አንድነታቸውን እንዴት ሊያስጠብቁ እንደቻሉ ነው፡፡ ከዮርዳኖስ መለስ የነበሩት ነገዶች በእግዚአብሔር ላይ ፈጽመውታል ብለው ባሰቡት አስከፊ በደል ምክንያት ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉትን ነገዶች ለመቅጣት ተዘጋጅተው ነበር የሄዱት፡፡ ሆኖም ሁኔታውን በጥበብ በመመርመር በመጨረሻም ለእግዚአብሔር በሚያቀርቡት አምልኮ ብሔራዊ አንድነታቸው እንደሚጠበቅ በማረጋገጣቸው ደስተኛ ሆኑ፡፡ እነዚህም ድርጊቶች በመጪው ዘመን በእስራኤል ነገዶች መካከል ግጭቶች ቢቀሰቀሱ ቀደምት ተደራሲያኑ እንዴት ሊፈቷቸው እንደሚገባ አደራረጉን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ጸሐፊአችን ቀጣዩን ትውልድ ለማስተማር ሲል ስለ ብሔራዊ አንድነት የዘገበውን ዘገባ ያዋቀረው በመጽሐፉ ውስጥ ደጋግሞ ያነሳቸውን አምስት መሪ ሃሳቦች በመጥቀስ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

## መለኮታዊ ሥልጣን

በመጀመሪያ ደረጃ፣ የመለኮታዊ ሥልጣን መሪ ሃሳብ ተጠቅሶ የምናገኘው በመሠዊው ግንባታ ወቅት ነው፡፡ በ22፡1 ውስጥ እንደምናስተውለው፣ ከዮርዳኖስ ማዶ የሚገኙ ነገዶች ወደ ርስታቸው እንዲመለሱ ያዘዘው ኢያሱ፣ በእግዚአብሔር የተሾመው መሪ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ ከዚህ ባሻገር፣ በቁጥር 13 ውስጥ የጦርነት ጥንስስ ሲከሰት በመለኮታዊ ሥልጣን የተሾሙት ፊንሐስ፣ እና የዓልአዛር ልጆች፣ ከዮርዳስ መለስ ያሉትን ልዑካን መርተው ሲሄዱ እናያለን፡፡

ጸሐፊአችንም የተደራሲያኑን አመለካከት ቅርፅ ለማስያዝ ሲል ትኩረቱን በኢያሱና በፊንሐስ ላይ እንዲደረግ ታሪኩን በዓላማ አዋቅሮታል፡፡ ስለዚህ ድርጊቱ እርባና የለሽ የቀደመ ታሪክ አድርገው እንዲቆጥሩት በፍጹም አይገባም ማለት ነው፡፡ ይልቁኑ በክንውኖቹ ውስጥ መለኮታዊው ሥልጣን በተግባር የመገለጡ ጉዳይ እነርሱም በዘመናቸው ችግር ሲገጥማቸው ከብሔራዊ አንድነታቸው አንፃር ይህንኑ መስመር እንዲከተሉ ያሳስቧቸዋል፡፡

## የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን

በሁለተኛ ደረጃ፣ በምዕራፍ 22 የሚገኘው ስለ ብሔራዊ አንድነት የሚያወሳው ታሪክ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳንም ይዳስሳል፡፡ መሪ ሃሳቡ ፊት ለፊት ተገልጦ የምናገኘው ከዮርዳኖስ መለስ ያሉ ነገዶች ልዑካን ከዮርዳኖስ ማዶ የሚገኙትን ፊት ለፊት በተጋፈጡበት ክፍል ውስጥ ነው፡፡ በቁጥር 25 እና 27 ውስጥ እንደምነብበው፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉት ነገዶች፣ የተቀሩት ነገዶች “እናንተ በምድሪቱ ላይ ምንም ድርሻ የላችሁም” እንዲሏቸው አልፈለጉም፡፡ “ድርሻ” የሚለው ቃል በዕብራይስጡ *cheleq* (חֵלֶק) የተባለው ቃል ፍቺ ነው፡፡ ኢያሱ 18፡7 እና 19፡9 የመሳሰሉ ክፍሎች እንደሚያሳዩን፣ ጸሐፊአችን *cheleq* (חֵלֶק) የተሰኘውን ቃል የሚያገናኘው “ውርስ” ወይም *nachalah* (נַחֲלָה) ከተሰኘው ቃል ጋር ነው፡፡ በዚህ ተከታታይ ትምህርታችን ደጋግመን እንዳየነው፣ “ውርስ” የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ የሚገናኘው እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሙሴ ከገባው ቃል ኪዳን ጋር ነው፡፡ ስለዚህ፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉት ነገዶች ይፈልጉ የነበረው በዮርዳኖስ በስተምእራብ የሚገኙት ነገዶች እነርሱንም ለአባቶቻቸው የተሰጠው የቃል ኪዳን ተስፋ ወራሾች አድርገው እንዲመለከቷቸው ነበር፡፡

የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገው ቀደምት ተደራሲያኑን ሊሞግታቸው በፈለገበት የብሔራዊ አንድነት ጉዳይ ጫን ማለት ስለፈለገ ነው፡፡ ቀደምት ተደራሲያኑን ሊያሳስባቸው የፈለገው የእስራኤል ነገዶች በጠቅላላ

በሰሜንም፣ በደቡብም፣ በምስራቅም ሆነ በምዕራብም ያሉት በጠቅላላ እግዚአብሔር በሰጠው ቃል ኪዳን መሠረት ከተስፋፉቱ ምድር ድርሻ ሊኖራቸው እንደሚገባ ነው፡፡

## የሙሴ ህግ ስነ-ልክ

በሦስተኛ ደረጃ፣ ጸሐፊአችን ስለ እስራኤል ብሔራዊ አንድነት ያሰፈረው ዘገባ በሙሴ ህግ ስነ-ልክም ላይ አጽንዖት አድርጓል፡፡ በትረካችን መግቢያ ላይ፣ ኢያሱ በዮርዳኖስ ማዶ ያሉትን ነገዶች በ22፡5 ላይ እንዲህ ሲል አስጠንቅቋቸዋል፡፡ "ብቻ የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ያዘዛችሁን ትእዛዙንና ሕጉን ታደርጉ ዘንድ… ተጠንቀቁ፡፡" በነገዶች መካከል በነበረው ሙግትም ወቅት፣ ከዮርዳኖስ መለስ ያሉት ነገዶች ልዑካንም በቁጥር 19 ላይ፣ "…ከአምላካችንም ከእግዚአብሔር መሠዊያ ሌላ ለእናንተ መሠዊያ በመሥራታችሁ በእግዚአብሔርና በእኛ ላይ አታምፁ።" በማለት አስጠንቅቀዋል፡፡ ያን ማድረግ ማለት የሙሴን ህግ መተላለፍ ማለት ነው፡፡ በቁጥር 29 ደግሞ፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉት ነገዶች ለሙሴ ህግጋት ያላቸውን ታማኝነት ሲያጸኑ "መሠዊያን የሠራነው በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ እግዚአብሔርንም ዛሬ መከተልን ለመተው በማለት እንደ ሆነ ይህ ከእኛ ይራቅ።" ብለዋል፡፡

ጸሐፊአችን በሙሴ ህግ ላይ የሰጠው አፅንኦት ብሔራዊ አንድነትን ከመጠበቅ አንፃር ወሳኝ ሆነን መመዘኛ ያስቀምጣል፡፡ ተደራሲያኑ ብሔራዊ አንድነታቸውን አጥብቀው መፈለጋቸው ወሳኝ የመሆኑን ያህል፣ ያንን ማድረግ ያለባቸው ግን በሙሴ ህግ በተቀመጠው መስመር መሠረት ሊሆን ይገባዋል፡፡

## የእግዚአብሔር ልእለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል

በአራተኛ ደረጃ፣ ስለ ብሔራዊ አንድነት የቀረበው ዘገባ በእግዚአብሔር ልእለ ተፈጥሮአዊ ኃይልም ላይ ትኩረት እንዲደረግ ያሳስባል፡፡ ይህ መሪ ሃሳብ በተለየ መንገድ ተገልጦ የምናገኘው ከዮርዳኖስ መለስ ባሉት ነገዶች ልዑካንና ከዮርዳኖስ ማዶ ባሉት ነገዶቸ መካከል በተካሄደው ሙግት መካከል ነው፡፡ ልዑካኑ በፌጎር በተሰራው ኃጢአት ምክንያት የተገለጠውን የእግዚአብሔር ቁጣ በማንሳት በቁጥር 17 ላይ፣ "በእግዚአብሔር ማኅበር ላይ መቅሰፍት ወረደ።" በማለት ስለ እግዚአብሔር ልእለ-መለኮታዊ ኃይል ማሳሰቢያ ሰጥተዋል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ፣ ፊንሐስ ከዮርዳኖስ ማዶ ያሉት ነገዶች የሰጡትን ማብራሪያ ካደመጠ በኋላ በቁጥር 31 ውስጥ የእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ባርኮት እንዲህ ሲል ገልጦታል "እግዚአብሔር በመካከላችን እንዳለ ዛሬ እናውቃለን፡፡"

እነዚህ የእግዚአብሔርን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ እርግማንና ባርኮት የሚያሳዩ ዘገባዎች የሚያሳስቡት ተደራሲያኑ በዘመናቸው ብሔራዊ አንድነታቸውን እንዲጠብቁ የቀረበው ጥሪ ሰብዓዊ ጉዳይ ብቻ እንዳልሆነ ነው፡፡ ልክ በኢያሱ ዘመን እንደሆነው ሁሉ፣ ብሔራዊ አንድነታቸውን ቢጠብቁ የእግዚአብሔር ባርኮት፣ መጠበቅ ቢሳናቸው ግን የእግዚአብሔር እርግማን ይጠብቃቸዋል ማለት ነው፡፡

## እስራኤል በጠቅላላ

በአምስተኛ ደረጃ፣ ይህ ስለ ብሔራዊ አንድነት የቀረበው ዘገባ እስራኤል በጠቅላላ በተሰኘው መሪ ሃሳብም ላይ ያስመረበት መሆኑን መገንዘባችን አስገራሚ አይሆንም፡፡ ገና በታሪኩ ጅማሬ ላይ ኢያሱ በቁጥር 3፣ 7 እና 8 ላይ በዮርዳኖስ ማዶና ማዶ የሚገኙትን እስራኤላውያን በጠቅላላ "ወንድማማቾች" ብሎ ሲጠራቸው መስሩ ቀድሞውኑ ተሰምሯል፡፡ በቁጥር 17 እና 20 ውስጥ ደግሞ፣ በሙግቱ ወቅት፣ በእስራኤል ውስጥ ጥቂቶች የሚፈጽሙት በደል በጠቅላላው የእስራኤል ማኅበር ላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ እንደሚያመጣ ልዑካኑ እውቅና ሰጥተዋል፡፡ ደግሞም በቁጥር 34 ውስጥ፣ አጠቃላዩ ትረካ የሚጠናቀቀው "እግዚአብሔር አምላክ እንደ ሆነ ይህ በመካከላችን ምስክር ነው" በማለት መሰዊያውን በሰየሙበት የእስራኤልን አንድነትና እምነት በሚያረጋግጠው ቃል ነው፡፡

በኢያሱ ዘመን በነበሩ የእስራኤል ነገዶች መካከል የነበሩት ውጥረቶች መፍትሄ ያገኙት በእስራኤል ነገዶች መካከል ላለው አንድነት በነበራቸው መሰጠት ምክንያት እንደነበር ጸሐፊአችን በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ ቀደምት

ተደራሲያኑም በእነርሱ ዘመን ለብሔራዊ አንድነት ተመሳሳይ የሆነ መሰጠት እንዲኖራቸው ጥሪውን ያቀርብላቸዋል፡፡

እስካሁን በተመለከትናቸው የትምህርታችን ክፍሎች የምድሪቱን ቀደምት ድንበር ታሳቢ በማድረግ ለእስራኤል ነገዶች የተደረገውን የርስት ክፍፍል፣ ለእስራኤል ነገዶች ለየት ባለ መንገድ የተደረጉ የርስት ድልድሎችን እና በነገዶቹ መካከል ሊገለጥ የሚገባውን ብሔራዊ አንድነት አስመልክቶ ጸሐፊአችን ያቀረበውንዳሰሳ አይተናል፡፡ አሁን ደግሞ የዚህ ትምህርት ማጠናቀቂያ ወደሆነው የመጨረሻ ክፍል ማለትም፣ የመጽሐፉን የዚህ ክፍል ክርስቲያናዊ ተዛምዶ ወደ መመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡

## ክርስቲያናዊ ተዛምዶ

የኢያሱ መጽሐፍ ይህኛው ክፍል የሚያቀርባቸው በርካታ ዝርዝሮች ዓላማ ተደርገው የተቀረፁት ለቀደምት ተደራሲያኑ ተግባራዊ መመሪያዎችን ለማስተላለፍ ነው፡፡ የቀደሙት አባቶቻቸው የተቀበሏቸውን ቀደምት ርስቶች አስጠብቆ ማቆየት ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ጸሐፊአችን ለተደራሲኑ ግልጽ ያደርግላቸዋል፡፡ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ነገድ የሰጠውን ለየት ያለ ድርሻ እንዴት ሊያከብሩት እንደሚገባ ያብራራላቸዋል፡፡ እስራኤላውያን በኢያሱ ዘመን ብሔራዊ አንድነታቸውን እንዴት እንዳስከበሩም በመገንዘብ እነርሱም ያንኑ እንዲያደርጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ታዲያ እኛስ ዛሬ ይህንን የእስራኤልን የነገዶች የርስት ክፍፍል ታሪክ የምናዛምደው እንዴት ነው? በቀላሉ ስናስቀምጠው፣ በኢያሱ ዘመን የተከናወነው ነገር እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት ለህዝቡ ያዘጋጀው የሚበልጥ ርስት አመልካች የሆነ የመጀመሪያ እርከን እንደሆነ ማስታወስ ይገባናል፡፡

የኢያሱን መጽሐፍ የዚህኛውን ክፍል ተዛምዶ የምንመለከተው ክርስቶስ በመንግሥቱ ግንባታ ሦስት እርከኖች ላይ እንዴት አድርጎ የእስራኤልን የነገዶች የርስት ክፍፍል ወደ ፍጻሜ እንዳመጣው በሚዳስስ መንገድ ነው፡፡ ይህም በመጀመሪው መምጣቱ ማለትም *በብሥራቱ፣* በቤተክርስቲያን የታሪክ ዘመን በተከናወነው *በእድገቱ* እና በሁለተኛው መምጣቱ *በፍጻሜው* ያከናወናቸውንና የሚያከናውናቸውን በመዳሰስ ነው፡፡ በክርስቶስ የመንግሥቱ ብሥራት የመጀመሪያ እርከን ብርሃን መሠረት የእስራኤልን የነገዶች የርስት ክፍፍል ከሕይወታችን ጋር እንዴት እንደምናዛምደው አስቀድመን እንመልከት፡፡

### ብሥራት

ክርስቶስ በመጀመሪያው መምጣቱ መሲሃዊ መንግሥቱን ሲያበስር እስራኤል ለበርካታ መቶ ዓመታት ከተስፋዪቱ ምድር እጅግ ርቃና ተበታትና ነበር፡፡ ወደ ከነዓን ምድር የተመለሱት እንኳን ሳይቀሩ ከአንዱ የአህዛብ መንግሥት ወደ ሌላኛው እየተቀባበሉ በጭቆና ስር ነበር ያኖሯቸው፡፡ ሆኖም በእስራኤል ምድር የነበሩት የታመኑት ሁሉ ግን በተስፋዪቱ ምድር ውስጥ የነበራቸውን ርስት መልሰው እንደሚያገኙት ባልወደቀ ተስፋ ይጠባበቁ ነበር፡፡ ደግሞም የእነርሱ ርስት በመሲሃቸው አማካይነት ተስፋፍቶ ዓለምን በጠቅላላ የሚሸፍንበትን ያንን ጊዜ በተስፋና በጉጉት ይጠባበቃሉ፡፡

> *እግዚአብሔር ለእስራኤል ርስትን እንደሚሰጣት የገባው ተስፋ ወደ ዔድን ገነት ይመለሳል፡፡ የሰው ዘር ዔደን ገነትን ብቻ ሳይሆን መላውን ዓለም ይገዛ ዘንድ እግዚአብሔር ለሰው ዘር በዔድን ገነት ውስጥ ተልዕኮ ሰጥቶት ነበር፡፡ እናም፣ በዚህ የመሬት ክፍፍልና ስጦታ ውስጥ የምናስተውለው፣ በምድር ሁሉ ላይ ገዢ የመሆንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ድንበሮች የማስፋፋት ተስፋ ሲያስተጋባ ነው፡፡ የዚህን ነገር ብልጭታውን የምናገኘው፣ በመዝሙር 2 እና 72 ውስጥ በተቀመጠው የዳዊት የንግሥና ቃል ኪዳን ውስጥ "ለምነኝ አህዛብን ለርስትህ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ" በተባለው ወይም በኢሳያስ ራእይ ውስጥ እስራኤል ለአህዛብ ሁሉ በረከት የመሆን ድርሻዋን ሲያመለክት "እባርክሃለሁ፣ የምድር ወገኖችም በአንተ ይባረካሉ" የተባለውን የአብርሃምን ቃል ኪዳን ያስተጋባል፡፡ ስለዚህም፣ በኢሳያስ 2 ውስጥ፣ መንግሥታት ሁሉ እንዴት አድርገው ወደ እስራኤል ማለትም ስለ ክርስቶስ ወይም ስለ መሲሁ በምትሰጠው ምስክርነት ተስበው እንደሚመጡ እናነብባለን፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፣ በአገልግሎቱ ውስጥ ያየነው ይህንኑ ሲሆን ያም እስራኤል ለአህዛብ ብርሃን ወደ*

*መሆን ተልዕኮዋ መመለስ ነው፡፡ በማቴዎስ ወንጌል መጨረሻ ላይ “ ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ … ደቀመዛሙርት አድርጓቸው፤ ያዘዝኋችሁንም እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤” ያለው ለዚህ ነው፡፡ ከዚያም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ “ምስክሮቼ ትሆናላችሁ” የሚለው ቃል በድጋሚ የሚያስተጋባው በኢሳያስ 43 ውስጥ፣ “በመንግሥታት ሁሉ መካከል ብቸኛው አዳኝ እኔ ብቻ መሆኔን ሂዱና ንገሩ” የሚለውን ቃል ነው፡፡ እናም ምድር የሚለው ቃል መላውን ዓለም የሚያመለክት ሲሆን እግዚአብሔር በመላው ዓለም ላይ ገዢ መሆኑን ያመለክታል፡፡*

*- ዶ/ር ግሬግ ፔሪ*

የኢየሱስ የመጀመሪያው መምጣት የገዢህ ተስፋ ፍጻሜ የመጀመሪያው ዋና እርከን መሆኑን አዲስ ኪዳን በግልጽ ያብራራልናል፡፡ ዕብራውያን 1፡2 እንደሚያብራራው፣ እግዚአብሔር ኢየሱስን “ሁሉን ወራሽ” አድርጎታል፡፡ ወይም ጳውሎስ በሮሜ 4፡13 እንዳስቀመጠው፣ ኢየሱስ “የዓለም ወራሽ” ነው፡፡ ደግሞም ከዚህ ባሻገር፣ ገላትያ 3፡29ን የመሳሰሉ ምንባቦች እንደሚነግሩን፣ “እናንተ በክርስቶስ ከሆናችሁ፣ እንደ ተስፋው ቃል ደግሞ ወራሾች ናችሁ” በሮሜ 8፡17 መሠረት፣ እኛ “ወራሾች… ማለትም በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሾች ነን” ይላል፡፡

ኢየሱስ በኢያሱ ዘመን በተሰጠው የነገዶች ርስት ክፍፍል መሠረት በእነዚያ ውስጥ እየተዘዋወረ ማገልገሉን አራቱ ወንጌላት የዘገቡት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ እርሱና ደቀመዛሙርቱ ከዮርዳኖስ መለስ በሚገኙት ሰሜናዊና ደቡባዊ ግዛቶች ውስጥ በመዘዋወር አገልግለዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ፣ ከዮርዳኖስ ማዶም አገልግለዋል፡፡ በዚህ ወቅት፣ ኢየሱስ ምድርን ከእርሱ ጋር የሚገዙትን፣ ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ የተውጣጡትን የእስራኤልን ቅሬታዎች ወደ እርሱ ይሰበስባል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ የሐዋርያት ሥራ 2፡5 እንደሚነግረን፣ በቅርቡ ወደ ሰማይ ያረገው ክርስቶ፣ “ከሰማይ በታች ካለው ሕዝብ ሁሉ” እርሱን የተከተሉትንና ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ የተውጣጡትን ወደ ኢሩሳሌም ሰብስቧል፡፡

ከሁሉም በላይ ግን፣ በእስራኤል የርስት ክፍፍልና በክርስቶስ መንግሥት ብሥራት መካከል ያለው እጅግ ወሳኝ የሆነው ግንኙነት በበዓለ ሃምሳ ቀን በቤተክርስቲያን ላይ የፈሰሰው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው፡፡ በኤፌሶን 1፡14 ውስጥ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን፡ “የርስታችን መያዣ” ሲል ገልጦታል፡፡ ደግሞም በ2ኛ ቆሮንቶስ 1፡22 እና 5፡5 ውስጥ፣ ጳውሎስ “መያዣ” ሲልም ገልጦታል፡፡ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን እንደ ተቀማጭ ወይም በክርስቶስ ወደ ፊት ለምንቀበለው ርስት ቀብዱ አድርጎ ለምን እንዳየው ለመረዳት ያስችለን ዘንድ በዘፍጥረት 1፡2 ወደተጠቀሰው ቃል በመሄድ፣ በመጀመሪያ ፍጥረትን ሁሉ ወደ ሥርዓት ያመጣው መንፈሱ መሆኑን ማየት ይገባናል፡፡ ደግሞም የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች፣ ለምሳሌ ኢሳያስ 44፡3-4 የመሳሰሉትን ስንመለከት፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በመሲሁ ዘመን ፍጥረትን ሁሉ ወደ ተሃድሶ እንደሚያመጣ ያብራሩልናል፡፡ በውጤቱም፣ በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ላይ የፈሰሰው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የዚህ የታደሰ ፍጥረት ቅምሻ ነው ማለት ነው፡፡ እርሱ በክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ሁሉ ነገር ተፈፅሞ እስክናይ ድረስ በመንግሥቱ ብሥራት ወቅት የተረጋገጠልንና የተቀበልነው ዓለም አቀፍ ርስታችንና ድርሻችን ነው፡፡

በዚህም ምክንያት፣ በኢያሱ መጽሐፍ በዚህኛው ክፍል ውስጥ ደጋግመን የምናገኛቸው እነዚህ መሪ ሃሳቦች በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የተቀበልነው ርስታችንን ቅምሻ እንድናጣጥመውና እርሱን እንድናስላስል ያደርጉናል፡፡ ልክ ኢያሱ በመለኮታዊ ሥልጣን በተስፋዪቱ ምድር ውስጥ ርስትን ለእስራኤል እንዳከፋፈለ ሁሉ፣ ኢየሱስ፣ ሐዋርያትና ነቢያትም በዚያው መለኮታዊ ሥልጣን ለሚያምኑ ሁሉ በመንፈስ የሆነውን ርስት አከፋፍለዋል፡፡ ልክ ኢያሱ ምድሪቱን በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መሠረት እንዳከፋፈለ ሁሉ፣ ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስን ላመኑት ሁሉ ማፍሰሱ እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት የገባው የአዲሱ ኪዳን ፍፃሜ ነው፡፡ በኢያሱ አማካይነት ለእስራኤል የተከፋፈለው ርስት የሙሴን ህግ ስነ-ልክ የጠበቀ እንደነበረ ሁሉ፣ የመንፈስ ቅዱስም መፍሰስ ክርስቶስ ኢየሱስ ለሙሴ ህግ ከነበረው ፍፁም መታዘዝ የተገኘ ሲሆን ያም ከሙሴ ዘመን በኋላ በሚመጣው የእግዚአብሔር መገለጥ ብርሃን መሠረት የተከናወነ ነው፡፡ የእስራኤል ርስት በእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል ላይ የተመሠረተ እንደነበረ ሁሉ፣ በኢየሱስ የመጀመሪያ መምጣት ወቅት መንፈስ ቅዱስ ሲፈስስ ከዚያ እጅግ የሚበልጥ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል በሥራ ላይ እንደነበር አዲስ ኪዳን በግልጽ ያስቀምጥልናል፡፡ በኢያሱ ዘመን የነበረውና እስራኤልን በጠቅላላ ያካተት የነበረው ቁም ነገርም እስከ መንግሥቱ ብሥራትም ድረስ ተስፋፍቶ ነበር፡፡ የታመኑት የእስራኤል ቅሬታዎቸ ብቻ ሳይሆኑ፣ አህዛብ አማኞችም ጭምር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የፈሰሰውን የክርስቶስን ውርስ ተቀብለዋል፡፡

የእስራኤል ነገዶች የርስት ክፍፍል ወደ ክርስቶስ መንግሥት ብሥራት እንዴት እንደሚወስደን የሚያመለክተንን ክርስቲያናዊ ተዛምዶ ከነካካነው፣ አሁን ደግሞ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከተገለጠውና ከሚገለጠው የመንግሥቱ መስፋፋት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ወደመመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡

## መስፋፋት

በክርስቶስ የመጀመሪና የሁለተኛ መምጣት መካከል፣ ክርስቶስ በመንፈሱ አማካይነት የምትመጣውን መንግሥት ቅምሻ ለህዝቡ መስጠቱን እያስፋፋው ነው፡፡ ኢያሱ በመጽሐፈ ኢያሱ እንደምናነብበው እስራኤላውያን ወደፊት በመግፋት የተስፋይቱን ምድር መውረሳቸውን እንዲቀጥሉ ጥሪ እንዳቀረበ ሁሉ፣ አዲስ ኪዳንም በመንፈስ ቅዱስ አማካይት ወደፊት እንድንገፋ ጥሪ ያቀርብልናል፡፡ እንደ ገላትያ 5፡16፣ "በመንፈስ ልንመላለስ"፣ እና እንደ ኤፌሶን 5፡18 ደግሞ፣ "በመንፈስ ልንሞላ" ይገባናል፡፡ በተጨማሪም፣ የኢያሱ ቀደምት ተደራሲን ለእያንዳንዱ ነገድ ለተሰጠው የርስት ድልድል እውቅና እንዲሰጡ ጥሪ እንደቀረበላቸው ሁሉ፣ የክርስቶስ ተከታዮችም ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አንጻር ተመሳሳይ ነገር ይጠበቅባቸዋል፡፡ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡4 እንደሚያስተምረን፣ "ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፣ መንፈስ ግን አንድ ነው፡፡" በተጨማሪም፣ ቀደምት ተደራሲያኑ በተስፋዪቱ ምድር ውስጥ በየርስቶቻቸው በሚኖሩበት ወቅት አንድነታቸውን እንዲጠብቁ ጥሪ ቀርቦላቸዋል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስም፣ በኤፌሶን 4፡3 ውስጥ የክርስቶስ ተከታዮች "የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ እንዲተጉ" ጥሪ አቅርቦላቸዋል፡፡

በዚህ ብርሃን መሠረት፣ በኢያሱ መጽሐፍ በዚህኛው ክፍል ውስጥ ያየናቸውን አምስቱን መሪ ሃሳቦች በምናስተውል ወቅት ሁሉ በእለት ከእለት ሕይወታችን ለክርስቶስ እንዴት መኖር እንደሚገባን የምናስተውልበትን እድል እናገኛለን፡፡ ከእስራኤል ርስት ጀርባ መለኮታዊ ሥልጣን እንዳለ ኢያሱ እውቅና እንደሰጠ ሁሉ፣ እኛም የዚህን ዓለም ጉዳይ ሳይሆን በክርስቶስ አማካይነት የተሰጠንን የመንፈስ ቅዱስ ርስት በመናፈቅ ለመለኮታዊው ሥልጣን እውቅና ልንሰጥ ይገባናል፡፡ እስራኤላውያን የመጀመሪያ ርስታቸው ባለመብትነት በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ እንደነበር ሁሉ፣ እኛም በአዲሱ ኪዳን በክርስቶስ ላገኘነው ድነት በመንፈስ ቅዱስ እንደታተምን እናምናለን፡፡ እስራኤላውያን ቀደምት ርስታቸውን ለሙሴ ህግ ስነ-ልክ ባላቸው ታማኝነት እንዳጸኑ ሁሉ፣ እኛም በአዲስ ኪዳን በተገኘው መገለጥ ብርሃን አማካይነት የሙሴን ህግጋት ተግባራዊ በማድረግ በመንፈስ ቅዱስ ባገኘነው ርስት ውስጥ እንኖራለን፡፡ የእስራኤል ርስት በእግዚአብሔር ኃይል የተረጋገጠ እንደነበር፣ የእኛም ርስት በፈሰሰው የመንፍስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት የተረጋገጠ ነው፡፡ ደግሞም እስራኤል በጠቅላላ በብሔራዊ ርስታቸው ተካፋይ እንደሆኑ ሁሉ፣ በምድር ላይ ከሚገኙ ህዝቦችና ነገዶች የተውጣጡ የክርስቶስ ተከታዮችም ተመሳሳይ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስን ርስት ይካፈላሉ፡፡

የእስራኤል ነገዶች የርስት ክፍፍል ክርስቲያናዊ ተዛምዶ የሚገናኘው ክርስቶስ በመንግሥቱ ብሥራት ወቅት ካከናወነው ተግባርና አሁን እኛ በምንኖርበት ዘመን እየተከናወነ ካለው የመንግሥቱ መስፋፋት ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ወደፊት ከምንጠብቀው ተስፋችንና በመንግሥቱ ፍጻሜ ከምንቀበለው ርስት ጋርም የሚገናኝና ያንንም በጉጉት እንድንጠብቅ የሚያደርገን ነው፡፡

## ፍጻሜ

እንደ ራእይ 21፡1 አገላለጽ፣ ኢየሱስ ዳግመኛ ሲመጣ "በአዲስ ሰማይና ምድር" ሁሉን እንደሚገዛ እኔም ሆንሁ እናንተ የተረጋገጠ ተስፋ አለን፡፡ የወደቀው ፍጥረት በእሳት ተቃጥሎ ይጠፋል፣ ክፋትም ይወገዳል፣ የእግዚአብሔርም መንግሥት በፍጥረት ሁሉ ላይ ይሰለጥናል፡፡ ይህ አዲስ ፍጥረት ግን የክርስቶስ ብቻ አይደለም፡፡ ከራእይ 21፡7 እንደምንረዳው፣ በዚያ ታላቅ ቀን እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ያውጃል፣ "ድል የሚነሳ ይህን ሁሉ ይወርሳል፡፡" እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ፣ አዲሱ ፍጥረት የእኛ የዘላለም ርስታችን ነው፡፡

> *በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ የምናገኘው ስለ ብሔራዊ ረስት የሚናገረው መሪ ሃሳብ ወሳኝ ርእስ ሲሆን፣ በዚህ ዘመን የምንገኝ ክርስቲያኖች ደግሞ በርካታ የምናዛምዳቸው ነገሮች አሉ፣ ምክንያቱም ስለ ተስፋዪቱ ምድር ተስፋ በኢያሱ ዘመን የተፈጸመው በገሚስ ስለሆነ ነው፡፡ ያም ማለት፣ በኢያሱ መጽሐፍ ውስጥ እንደምናየው፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም እሰጥሃለሁ ብሎ ተስፋ የገባለት ምድር በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጡ ከነዓን ብለን*

*በምንጠራው ምድር ብቻ የሚወሰን አይደለም፡፡ በሮሜ 4፡13 "የዓለምም ወራሽ እንዲሆን ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል በእምነት ጽድቅ ነው እንጂ በሕግ አይደለም።" የሚል ቃል እናነብባለን፡፡ ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚነግረን አብርሃም ዓለምን ማለትም መላውን ዓለም እንደሚገዛ ነው፡፡ ደግሞም እነዚህ ተስፋዎች ለአህዛብም ጭምር ማለትም በሥጋ የአብርሃም ዘር ላልሆኑት፣ ግን በክርስቶስ፣ ራሱ የአብርሃም ዘር በሆነው በኩል ተስፋውን በእምነት ለተቀበሉትም ይፈጸማሉ፡፡ ስለዚህ፣ አብርሃም የተቀበለው ደግሞም እስራኤል በኢያሱ ዘመን የተቀበለችው የዚህ ትልቅ ባርኮት ትንሽ ክፍል ሲሆን፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገበው ተስፋ በበለጠ መጠን የተፈጸመው በክርስቶስ ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ የሚፈጸመው ግን ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ ነው፡፡ በስተመጨረሻም፣ ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ፣ የሚነግሠው በከነዓን ምድር ብቻ ሳይሆን፣ የሚነግሠውና የሚወርሰውም መላውን ዓለም ነው፡፡ ያም ዓለም አዲስ ሰማይና ምድር ሲሆን እኛም ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም እንነግሣለን፡፡*

*- ሬቨረንድ ሸሪፍ ጌንዲ፣ ትርጉም*

በዚህ ምክንያት፣ በኢያሱ መጽሐፍ በዚህኛው ክፍል ውስጥ የምናገኛቸው አምስት ዋና ዋና መሪ ሃሳቦች በክርስቶስ መንግሥት ፍጻሜ ወደ ምናገኘው ተስፋ ዓይናችንን እንድናቀና ያደርገናል፡፡ ኢያሱ በዘመኑ ያከናወነው ነገር በመለኮታዊው ሥልጣን የተጠበቀ እንደነበረ ሁሉ፣ ኢየሱስም ዳግመኛ በክብር ሲመለስ እግዚአብሔር የሰጠንን ተስፋ በፍፁምነት ሙሉ ለሙሉ ያከናውንልናል፡፡ የእስራኤል ወራሽነት በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የተጠበቀ እንደነበረ ሁሉ፣ የእኛም ውርስ በክርስቶስ በሆነው አዲስ ኪዳን የተረጋገጠ ነው፡፡ ኢያሱ የእስራኤላውያንን ርስት በሙሴ ህግ ስነ-ልክ መሠረት እነዳከፋፈለ ሁሉ፣ የክርስቶስ ተከታይ የሆኑት ሁሉ በሙላት የክርስቶስን መልክ ያንጸባርቃሉ ደግሞም በሚመጣው ዓለም የሚገለጠውን መለኮታዊ ስነ-ልክ በሙላት ይፈጽማሉ፡፡ እስራኤል ውርሷን የማግኘቷ ነገር ከእግዚአብሔር ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል እንደመነጨ ሁሉ፣ ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣም፣ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ መጠን እግዚአብሔር ኃይሉን ይገልጣል፡፡ የእስራኤል ርስት እስራኤላውያንን በጠቅላላ እንደሚያካትት ሁሉ፣ በክርስቶስ የሆኑት ሁሉ በሚመጣው ዓለም የዘላለም ርስታቸውን ይቀበላሉ፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት፣ በኢያሱ መጽሐፍ ሁለተኛ አጋማሽ ውስጥ የሚገኘውን የእስራኤልን የነገዶች የርስት ክፍፍል ቃኝተናል፡፡ ጸሐፊአችን እስራኤል ከዮርዳኖስ ማዶና ከዮርዳኖስ መለስ የተቀበለችውን ምድር በማብራራት እስራኤል ጥንት ለተቀበለችው ድንበር እንዴት አድርጎ ቅድሚያን እንደሰጠ ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም በኢያሱ ዘመን የተከናወኑትንና ከዮርዳስ ማዶና ከዮርዳኖስ መለስ የሚገኙትን ለየት ያሉ የነገዶች ርስት ክፍፍሎችም ዳስሰናል፡፡ እስራኤላውያን በኢያሱ ዘመን እንዴት አድርገው አንድነታቸውን አስጠብቀው እንደቆዩ በማብራራት፣ የእስራኤል ነገዶቸ በጠቅላላ ብሔራዊ አንድነታቸውን ሊያስጠብቁ እንደሚገባ ጸሐፊአችን ያቀረበውን ሙግትም አይተናል፡፡ በመጨረሻም፣ ይህን የኢያሱን መጽሐፍ ክፍል ከክርስቶስ መንግሥት ብሥራት፣ እድገትና ፍጻሜ አንፃር የሚኖረውን ክርስቲያናዊ ተዛምዶም ጭምር ተመልክተናል፡፡

የኢያሱ መጽሐፍ ጸሐፊ በኢያሱ አመራር እግዚአብሔር ያከናወናቸውን ተግባራት ተደራሲያኑም የማረጋገጣቸውንና የማስከበራቸውን ወሳኝነት ለተደራሲያኑ ጫን አድርጎና አስደምሞ አቅርቦታል፡፡ ዛሬም እኛ፣ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ተመሳሳዩን ማድረግ ይገባናል፡፡ እኛም ኢየሱስ ዘላለማዊ ርስታችንን እንዳስገኘልን እናውቃለን፡፡ እለት በእለትም፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የዚያን ርስታችንን ቅምሻ እያጣጣምን እንኖራለን፡፡ ደግሞም ክርስቶስ በክብር የሚመለስባትን ያችን ቀን በጉጉት እንጠባበቃለን፡፡ በዚያም ቀን፣ ሁሉን ወራሽ የተደረገበትን ሥልጣኑን ይረከባል በአዲሲቷ ምድርም በእርሱ ለታመኑ ሀሉ ከዚያ ትልቅ ርስት ለዘላለም ለሁሉ ያወርሳል፡፡